

ዋጋ ፩ ብር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

# ንሣት



ወንጌላዊው ማቴዎስ

ቁጥር ፰፴

መስከረም ፲፱፻፹፩ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጉሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።»


ዋና አዘጋጅ
ሊቀ ጉባኤ [illegible]

ም. አዘጋጅ [illegible]
[illegible]

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና [illegible] ቅልስክ መምሪያ
[illegible] ክፍል [illegible]
በዓመት አንድ ጊዜ
[illegible] የሚታተም

ስልክ ቁጥር 110754
መልእክት ሣ. ቁ. 3[illegible]
አዲስ አበባ


# ማውጫ

**ገጽ**

እርእሶች


ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ (እንኳን ለአዲሱ ዘመን አደረሳችሁ) ........ ፪
ልብህን ስጠኝ ........ ፬
ዘመን ሐዲስ ........ ፭
[illegible] (ዮሐንስ መጥምቅ) ........ ፯
ዜና ሊቃውንት ........ ፱
ትዕግሥት እንደ ኢዮብ ........ ፲
[illegible] ወንድሞቻችን [illegible] የዛሬ መዳኛ ........ ፲፩
[illegible] በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፪
ዜና ዕረፍት ........ ፲፬
መናፍቃንን መዋጋት ........ ፲፯
[illegible] በረከት ........ ፲፰
[illegible] ትምህርት ጥቅሙ ........ ፲፱
[illegible] ........ ፳፪


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
<u>አዲስ አበባ</u>

በተቀዳሚ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ለሚቀርቡላችሁ ጥያቄዎች በምትሰጧቸው መልሶች በጣም ደስ ይለኛና እኔም በበኩሌ ለመጠየቅ ሁልጊዜ እመኛለሁ ነገር ግን መልስ ያልሰጣችሁኝ እንደሆነ ቅሬታ ይገባኛል በማለት ከአሁን ቀደም ጥያቄ ጽፌ አላውቅም ቢሆንም የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታይ እስከሆንኩ ድረስ መጠየቁ የሚያሳፍር መስሎ አልታየኝም ስለዚህም የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቅርቤያለሁና መልሳችሁን እንድትሰጡኝ በትሕትና እለምናለሁ ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ አንድ አገልጋይ በአንድ ጊዜ ለሁለት ጌቶች ለመታዘዝ ይቻለዋል?

፪ኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ምእመናንን ነው ?

ወይስ ገንዘባቸውን ?

፫ኛ በአሁኑ ጊዜ ብዙ የሃይማኖት ክፍሎች እንዳሉና ለሁሉም የግል አምልኮት መፈጸሚያ የጸሎት ቤቶች አሏቸው ይሁን እንጂ አንድ ክርስቲያን አባል መሆን የሚገባው ለስንት አብያተ ክርስቲያናት ነው ?

፬ኛ ሁለት ባልና ሚስት ክርስቲያኖች በአንድ ላይ እየኖሩ ባልየው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን ሚስቱ ለሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን ይገባታልን?

፭ኛ በአዲስ አበባ ከተማም ሆነ በየአህጉረ ስብከቱ በርከት ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ታንፀዋል ፤ በዘመን ብዛት ያረጁትም ታድሰዋል በመታደስም ላይ ይገኛሉ ። ነገር ግን አንዳንድ የሰበካ ጉባኤ አባላት የድሳትና የዕድገት ኮሚቴዎች እየተባሉ የሚመረጡት ሰዎች ሕዝበ ክርስቲያኑ የወንጌልን ቃል ሰምቶ እንዳይጠቀም ለመምህራኑም ሆነ ለእኛ ለሰሚዎች ክርስቲያን እንቅፋት ሆነውብናልና ምክሩልን እባካችሁ የእናንተን ምክር እንሰማም እንቀበልም ካሉ ደግሞ ሻሩልን ለእኛ ለምእመናን የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ ይበቃናልና አስተዳዳሪው የሚያዝዘንን ሁሉ በደስታ እየተቀበልን እንፈጽማለን ፤

፮ኛ በስብከተ ወንጌል መምሪያ አማካይነት የሚታተሙ መጽሔቶችና ጋዜጦች እንዲሁም ልዩ ልዩ መጻሕፍት መኖራቸው የታወቀ ነው እነርሱን ለምእመናን ለማሰራጨት ሰባክያን በየአብያተ ክርስቲያናቱ በሚዘዋወሩበት ጊዜ አንዳንድ ጥቅሙና ዓላማው ያልገባቸው የአብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ ተመራጮች ሳይቀሩ ለመተባበር ፈቃደኞች ሆነው አይታዩም ። የጋዜጦችንና የመጽሔቶችን ጥቅም በሰፊው ለማስረዳት የአንድ ቀን ሴሚናር ለምን አይደረግም?

፯ኛ የመጽሔቶችና የጋዜጦች ብዛት አነስተኛ ስለሆነ ብዙዎች ምእመናን ለማንበብ ፍላጎት እያላቸው ሊያገኙ አልቻሉም ለምን ቁጥራቸው እንዲጨምር አይደረግም ?

ከምእመናን አንዱ መስፍን ገብረ ትንሣኤ

አቶ መስፍን ገብረ ትንሣኤ ስለአቀረቡልን መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰገን ላቀረቡልን ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን ።

የመጀመሪያው ጥያቄ አንድ አገልጋይ በአንድ ጊዜ ለሁለት ጌቶች ለመታዘዝ ይችላልን የሚል ነው ። የዚህ መልስ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፮ ቁጥር ፳፬ ላይ ተጽፏል ቃሉም የሚከተለው ነው !! አንድ ሰው ለሁለት ጌቶች አገልጋይ ሊሆን አይችልም አንዱን ይጠላል ሌላውን ይወዳል አንዱን ያከብራል ሌላውን ይንቃል !! ይላል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን ትምህርት ያስተማረው ለገንዘብና ለእግዚአብሔር መገዛት እንደማይቻል ቢሆንም በዚህ ዓለምም ለሁለት ሰው በአንድ ጊዜ ለማገልገል እንደማይቻልም የሚያስረዳ ነው ስለዚህ መልሱ አይቻልም ነው ።

ሁለተኛው ጥያቄ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ምእመናንን ነው? ወይስ ገንዘባቸውን ነው ? የሚል ነው። የዚህ ጥያቄ በአጭሩ መልሱ የምትፈልገው በመጀመሪያ ምእመናንን ነው ። ምእመናንና ቤተ ክርስቲያን አንድ ከሆኑና ከተስማሙ የቤተ ክርስቲያን ንዋያት እነርሱ ናቸውና ችግር አይኖርም ።

ሦስተኛው ጥያቄ አንድ ክርስቲያን ለስንት አብያተ ክርስቲያናት አባል መሆን እንዳለበት የሚሳስብ ነው ። በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን አንዲት ናት ከጊዜ

(ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል)



www.ethiopianorthodox.org

(ርእሰ አንቀጽ)

# እንኳን ለአዲሱ ዘመን አደረሳችሁ

አድራሹ ፈጣሪ ደራሾቹ ፍጡራን ናቸው መዓልት አልፎ ሌሊት ይተካል ሌሊት ሲያልፍ ደግሞ ተተኪው መዓልቱ ነው እንዲሁም ክረምትና በጋም በወቅታቸው ይፈራረቃሉ ወደሰውም ተፈጥሮ መለስ ብለን ስንመለከት በተፈጥሮው ጸንቶ የሚኖር አንድም ሰው አናገኝም ሰው ይወለዳል ያድጋል ይጉለምሳል ከዚያም በኋላ ያረጃል ያፈጃል በመጨረሻም ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል።

ይሁን እንጂ እንደሞተ ፈርሶ በስብሶ ለሁልጊዜ አይቀርም በኋለኛው ዘመን (በዕለተ ምጽዓት) በሐዲስ ሥጋ ተነሥቶ አዲስ መንግሥተ ሰማያትን ወርሶ በተሐድሶ ጸንቶ የመኖር ተስፋ አለው ።

ዘመን ግን በየዓመቱ አዲስ የሚለውን ቅጽል እየተቀዳጀ ይኖራል ። አንዱ ዓመት 365 ቀኖችን በውስጡ የሚይዝ ሲሆን በአምስተኛው ዘመን በዘመነ ሉቃስ 366 ቀኖችን ይዞ ይገኛል ። እነዚህ ቀኖች ሲፈጸሙ እንደገና አንድ ተብሎ ይጀመራል ። አንድ ተብሎ የሚቆጠረውም የመጀመሪያ ቀን የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ነው ።

ሰው ዓመት ሙሉ የሠራውን ሥራ በማስታወስ ለሌላ ሥራ በአዲስ ዝግጅት ለመሥራት ታጥቆ የሚነሣው በአዲሱ ዘመን መጀመሪያ ላይ ነው አንድ መጽሐፍ አንባቢ መጽሐፉን ሲያነብ ቆይቶ ከምዕራፍ በደረሰ ጊዜ በአነበበው መጽሐፍ ውስጥ ያገኘውን ኃይለ ቃል የተረዳውን ምሥጢር ለማስታወስ ትንሽ አረፍ እንደሚል ዘመን አልፎ ዘመንም ሲተካ ባለፈው ዓመት ምን ሥራ ሠራሁበት በተጀመረውስ አዲስ ዘመን ምን ዓይነት ሥራ እሠራበታለሁ ብሎ ማሰብ ማውጣትና ማውረድ የእያንዳንዱ ሰው ዓላማ ሊሆን ይገባል ።

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ ጀምሮ ያለፉት ዓመታት እንደኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አቆጣጠር 7.481 ናቸው ። ወደፊት እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ዘመናት እያለፉ ዘመናት በተተኩ ቁጥር ከዘመናት ጋር አብረው የሚያልፉ ደመነፍስ ያላቸው ፍጥረታት ናቸው በምድር ላይ የሚገኙትን ፍጥረታት እንደአስፈላጊነታቸው እንዲጠቀምባቸው እግዚአብሔር ለሰው በሥነፍጥረታት ላይ የበላይነቱን ሥልጣን ስለሰጠው ወቅቱን እየጠበቀ አዝርዕትን በመዝራት አትክልትን በመትከል እንስሳትንም በማርባት ይጠቀማል ።

ሰው የሆነ ሁሉ ስጦታው አንድ ዓይነት አይደለም እንደመልኩ ለሁሉም የተለየ ስጦታ አለው ለአንዱ ነገዶ የማትረፍ ስጦታ ሲኖረው ለሌላው ደግሞ አርሶ ቆፍሮ ዘር ዘርቶ ተክል ተክሎ የማምረት ስጦታ ሊኖረው ይችላል ። ለማስረጃ ያህል ጥቂቶቹን ጠቀስናቸው እንጂ ሰው ተሰማርቶ የሚሠራባቸው የሥራ ዓይነቶች አያሌ ናቸው ።

በተለይ በዘመነ ክረምት ገበሬዎች ለአዝርዕት ለአትክልት በብርቱ የሚጥሩበት ሲሆን ከዘመን መለወጫ ወዲህ ደግሞ የበቀሉትን ቡቃያዎች የሚያርሙበት የሚንከባከቡበት ከአይጥ ከጉርጥ ከለውሬው ከከብቱ በንቃትና በትጋት የሚጠብቁበት ነው ። የአንዱን ዓመት ኑሮ ጨርሰን አዲሱን ዓመት ከጀመርን ጥቂት ቀኖች አልፈዋል ።

ያለፈው ዘመን ዮሐንስ ነበር አሁን የተጀመረው ዘመነ ማቴዎስ ነው የተዘሩት አዝርዕት የተተከሉት አትክልት ለፍሬ የሚበቁት ወደፊት በሚቀጥሉት ወራቶች ስለሆነ ወራቱን ባርኮ ቀድሶ እንዲሰጠን አትክልት ለፍሬ የሚበቁት ወደፊት በሚቀጥሉት ወራቶች ስለሆነ ወራቱን ባርኮ ቀድሶ እንዲሰጠን የተዘሩትን አዝርዕትና የተተከሉተን አትክልት ለፍሬ እንዲያበቃልን ወደፈጣሪያችን መጸለይ ይገባናል ።

እግዚአብሔር በዓለም ሳለን መልካም ሥራ እንድንሠራ እንጂ ዓለሙን እንድንጠላው ለላዘዘንም እንዲያውም እንዳንሰለቸውና ደስ እያለን እንድንኖርበት ወቅቶቹን በመለዋወጥ ይመግበናል ። ለምሳሌ በመስከረም ወር ብዙ አዳዲስ ነገሮችን በዓይናችን እንመለከታለን መሬት በቅጠልና በአበባ በአትክልትና በአዝርእት ተሸፍና እውኝ እውኝ ተመልከቱኝ ዓይናችሁን ከእኔ አትመልሱ አንገታችሁን ወደሌላ አትቀልሱ ትለናለች ። ወንዞች ከአፍ እስከ ገደፋቸው ሞልተው መንገደኞችን ለላስተላልፍ ሲሉ የነበሩት አሁን እየጉደሉ ማሳለፍ ይዘዋል መልካቸውም ደፍርሶ ጭቃ ሆኖ ይታዩ የነበሩት እንደዮር ዓይን ኮለል ብለው ጠርተው እንኳን የጠማውን ያልጠማውንም ሰው ያለልቡ ጠጡኝ ጠጡኝ የሚል ስሜትን ያሳድራሉ ። እነዚ ጋራዎችና ሸንተረሮች ሁሉ በአበባ በቅጠል ተሸልመው ይታያሉ ወደላይም ቀና ብለን ስንመለከት በደመና ተሸፍኖ የከረመው ሰማይ አንዳንድ ጊዜ ፊቱን ገልጥ በማድረግ ከዋክብት ሲያበሩ እንመለከታለን በዝናብ በጉርፍ በውኃ ሙላት በጭቃ ምክንያት ተዘግተው የነበሩትም ት ቤቶች ተከፍተው ሥራቸውን በመቀጠል ላይ ይገኛሉ ። መብረቅና ነጐድጓድም ትዕግሥትንና አርምሞን በማዘውተር ላይ ናቸው አልፎ አልፎም ገበሬዎች እሸት እየቈረጡ በመቅመስ ላይ ይገኛሉ ፤

እነዚህንና የመሳሰሉትን ስንመለከት ሐዋርያው ዮሐንስ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ ብሎ እንደተናገረው እኛም የእርሱን ቃል መሠረት በማድረግ በዚህ ወቅት ስለምንመለከታቸው አዳዲስ ነገሮች ከሐሊ አምላካችን ከልብ እናመሰግናለን ቸርነቱ የማያልቅ እግዚአብሔር አምላካችን ዘመንን እያደሰ አዳዲስ ነገሮችን ያቀርብልናል እርሱ የሚሰጠንን እየተቀበልን ዝም ብለን በአርምሞ መቀመጥ አይገባንም።

የእኛም ሰውነት እንዲታደስ ማድረግ ይገባናል ሰውነታችን እንዲታደስ የምናደርገው በምንድን ነው ? የእኛ ሰውነት ሊታደስ የሚችለው አዳዲስ ልብስ በመልበስ ብቻ አይደለም ወይም አዳዲስ ምግቦችን በመመገብ ተሐድሶተ ነፍስን ለማግኘት አንችልም ።

ለእኛ የሚያስፈልጉን ተሐድሶዎች በሁለት መንገዶች የተከፈሉ ናቸው እነርሱም አንደኛው የሥራ ሁለተኛው የነፍስ ናቸው ። የነፍስ ተሐድሶ በንስሐ ሲሆን የሥጋ ተሐድሶ ደግሞ ሥራ ነው ። የቆየ ስንፍና እንዳለብን አስወግደን በንቃትና በትጋት ሆነን በአዲስ ጉዳና መራመድ አለብን ባለፈው ዓመት የሠራነው ሥራ ጥቅም አልሰጠን ብሎ እንደሆነ አሻሽለን በመሥራት መልካም ውጤት ለማግኘት መታገል ያስፈልገናል።

በነፍሳችንም በኩል ሃይማኖታችንና ምግባራችንን አጠንክረን ኃጢአታችን በንስሐ የማስወገድ መንፈሳዊ ግዴታ አለብን አሮጌውን ኃጢአት ሳናቃልል እንደተሸከምን ወደ አዲሱ ዘመን ማለፍ አይገባንም ። አሮጌውን ተዉት አዲሱን ልበሱት ተብሎ እንደተጻፈው አሮጌውን ዘመን ከሮጌው ሥራ ጋር ትተን በአዲሱ ዘመን በአዲስ ግብር እንመላለስ ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላም ያደረሰን አምላክ ከሚቀጥለው ዘመን በሰላም ያድርሰን ።



## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፳፩ የዞረ)

የሚገባው ታላቅ ስሕተት በመሆኑ ለትምህርተ ወንጌልም ጊዜ እንዲሰጡ መንፈሳዊ መልእክታችንን እናስተላልፋለን ።

ጠያቂው ምክሩን ካልሰሙ ሻሩ ልን ብለዋል እኛ ሺሚዎችና ሻሪዎች ስላይደለን የሚመለከተው ክፍል ያስብበት እንላለን ፤

እንዲሁም የሚታተሙት መጽሔቶችና ጋዜጦች በሚሸጡባቸው ወቅት ካህናትም ሆኑ የሰበካ ጉባኤ ተመራጮች ስለማይተባበሩ ሰሚናር ቢደረግላቸው የተሻለ መሆኑን አሳስበዋል ። በዕርግጥ ጠያቂው እንዳሳሰቡት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አዳራሽ በየጊዜው ሲሚናር ይደረጋል ግን በሲሚናሩ የሚነገረውን በሥራ ለመተርጐም አልቻሉም በተጨማሪም የሰበካ ጉባኤ ስምሪት በሚደረግበት ሁሉ ልዑካኑ ስለጋዜጦችና መጽሔቶች ጥቅም እንዲያስረዱ ተደርጓል ይህ ሁሉ ሆኖ ጥቅሙ የገባቸው ጥቂቶች ናቸው ጠያቂው እንዳሉት ሲሚናርም እናደርጋለን ለዚህ ተግባር ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት እንዲተባበሩም እናሳስባለን ፤

አቶ መስፍን በመጨረሻው ጥያቄ የጋዜጦችና የመጽሔቶች ብዛት እንዲጨምር ጠይቀዋል እኛም ቀደም ብለን ጉዳዩን ተረድተን ለበላዮቻችን አሳስበናል በተፈቀደ ጊዜ በብዛት ሊታተሙና ለምእመናን ሊዳረሱ ይችላሉ እስከዚያው ግን በትዕግሥት መጠበቅ ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ልብህን ስጠኝ

ልብ የፍጥር መንሻና መድረሻ መሆኑን የተገነዘበውና ታላቅ አገልግሎት መስጠቱን የተረዳው መንፈሳዊ ጸሐፊ የነበረው ጠቢቡ ሰሎሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ ፳፫ ቁጥር ፳፮ የጻፈው ይህ አባባል በየጊዜው ስለሚነገው ትውልድ ሁሉ መልካም ትምህርት ሆኖአል ። አባቱም ዳዊት ቢሆን ሐሳቡ ስላረጀ ፍርድና ተግባሩም ስለተዛባበት ሕይወቱም ስለጎሰቆለበት ነገር አዋቂና ፍርድ ጠንቃቂ እንዲሆን ሐሳቡ ተለውጦ ከአሮጌ ህይወት ወደ አዲስ ህይወት እንዲሸጋገር "አቤቱ ንጹህ ልብን ፍጠርልኝ የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ" ሲል እንደዘመረ እናገኛለን መዝሙር ፶ ቁጥር ፲ ፡

መዝሙረኛው በኀጢአትና በበደል ያረጀውንና የጎሰቆለውን ልቡን በንስሐ ስላደሰ ሐሳቡ ሥራውም አዲስ ሆነለት ፡ በጎ ነገርም እየሠራ ባለ ታሪክ ለመሆን በመብቃቱ ልብ የሚሰጠውን አገልግሎትና ለሰውነት ሁሉ መሪ ኃይል እንዳለው በነገሩ መስክሮአል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እየተዘዋወረ በሚያስተምርበት ጊዜ መዝገብህ ባለበት በዚያም ልብህ አብሮ ይኖራል ሲል ተናግሮአል ይህም አባባል ልብ ለሥራ ሁሉ ሐላፊ መሆኑንና መሪነትም እንዳለው ያረጋግጣል ። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፪ ቁጥር ፴፬ ደግሞ በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል ፡ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ልቡ ክፉ ነገርን ያወጣል" ሲል ከልብ ክፉ ነገርና መልካም ነገር እንደሚመነጭ አስተምሮአል ፡ ቀጥሎም ደቀ መዛሙርቱን ልባችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በኔም ደግሞ እመኑ ሲል ሥጋዊ ሥራ ብቻ ሳይሆን የእምነትና የምግባርም ሐላፊ ልብ መሆኑን ነግሮአቸዋል፡ ልብ ከፈራ ደግሞ በመላ ሰውነት ፍርሐት እንደሚሰራጭ ጨምሮ ነግሮአቸዋል ።

ከዚህ የተነሳ ስለ ልብ ሠራተኛነት አስተዋይነት ፍቅርም በልብ ላይ እንደሚመነጭ በየጊዜው የተነሱ ደራሲያን በድርሰታቸው ጽፈዋል ። ባለቅኔዎችም በብዛት ተቀኝተዋል አበውም ቢሆኑ ልዩ ልዩ ምሳሌ እየመሰሉ ለትውልድ አበርክተው አልፈዋል ። ከምሳሌዎቻቸው ጥቂቶቹን ብንጠቅስ አንደኛ ልብ እንደ ጎራዴ ተመዞ የሚታይ ቢሆን ኖሮ የቆራጥ ጀግና ልብ በአደባባይ ታይቶ በተመሰከረለት ነበር ሁለተኛ ልብ ካላየ ዓይን አያይም ሶስተኛ አፉ ነው እንጂ እገሌ ልቡ የዋህ ነው ። አራተኛ እገሌ ፈሪ ነው ልብ የለውም ቢገኝ ገበያ ብንገዛለት ይሻላል እኒህና እነዚህን የመሳሰሉ አያሌ ምሳሌዎች አሉ ።

በተጨማሪ ዓይን ለሰውነት መብራት እንደሆነ ሁሉ ልብም ልዩ ልዩ ሐሳብን እያመነጨ ለሰውነት እንደሚያሰራጭና አስተያየትንም እየፈጠረ እንደሚያስተላልፍ የትውፊት ወይም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው አባባልና ቅዱሳት መጻህፍትም ቢሆኑ ይመሰክሩለታል ። በዚህ አኳኋን መውደድ ፡ መጥላት ፡ ማስታወስ ፡ መርሳት ፡ ፍርሐት ፡ ድፍረት ፡ መስጠት ፡ መንሳት ፡ መንቃት ፡ መስነፍ ፡ በጠቅላላው ምሥጢር የመሰወርና የማውጣት ስጦታ ሁሉ የልብ ጠባይ መሆኑ እስከ ብዙ ዘመን ድረስ ታውቆ ኖሮአል ዘማርያንም ቢሆኑ ልብ የፍቅር ባለቤት መሆኑን ብዙ ዘምረዋል ከዘመሩአቸውም መካከል ጥቂቶችን ወደ ስድ ለውጠን ጥቂቶቹን እናቀርባለን ።

ልቡን ለመምታት ሎሚ ብወረውር ያልፈለኩትን ደረቱን መታው ልቡን ባገኘው ኖሮ ጥሩ ነበር ልብህን ስጠኝ ልብሽን ስጪኝ በልብ የከበሩ ሰዎች ስለሉሉ ልብሽ ይበልታኛልና ልቤን መልሽልኝ ልቤን የሰጠሁሽ በቁርባን በተክሊል እንጋባለን ብዬ ነበር በዚህ ከተስማማሽ አንድ አካል አንድ ልብ ስለምንሆን አንቺ ጋር ተቀምጦ ይቆየኝ በዚህ የማትስማሚ ከሆነ ልቤን በሰንሰለት አስረሽ ወደኔ መልሽልኝ ። ልቤ ልምከርህ አንዷት ሴት ላንድ ወንድ አንድ ወንድ ላንዷት ሴት መጽሐፉ ስለሚል በየመንገዱ ያየኸውን ሁሉ አትውደድ ትርፉ በሽታና ኩነኔ ነው የሚል ነው ።

ልብህን ስጠኝ የሚለው አባባል በቀድሞው ዘመን አንድ ሰው በጣም ሀብታም የሆነ ወዳጅ ነበረው ስለችግሩ ሄዶና እጅ ለእጅ ተጨባብጠው በእጅህ እንደጨበጥከኝ በልብህ ጨብጠኝ ልብህንም ስጠኝ አለው ። ባለፀጋው በንግግሩ ግራ ስለተጋባ ገንዘብ ብትጠይቀኝ ካለኝ የገንዘብ ግጥን ከወርቁም ከገንዘቡም እሰጥህ ነበር ልብስ ብትጠይቀኝ እንደ ዚሁ አደርግልህ ነበር እህልም ብትጠይቀኝ ከጎተራዬ የፈለከውን እህል እንድትወስድ እፈቅድልህ ነበር ። ያንተ ጥያቄ ግን ልብህን ስጠኝ የሚል ስለሆነ ነገሩ



አልገባኝም አለው ጠያቂውም ልብህን ስጠኝ ማለቴ ከሆድህ አውጥተህ ስጠኝ ማለቴ አይደለም ከልብህ ውደደኝ ማለቴ ነው ቢለው ከልቤማ እንደምወድህ ታውቅ የለም ወይ ሲል መለሰለት ከልብህማ ከወደድከኝ ልብህን ስጠኸኝ ማለት ስለሆነ ሀብትህ ገንዘብህ ይቅርና አንተው እራስህ የኔነህ ሲል ነገረው ይባላል ።

በርዕሱ እንደጠቀስነው ጠቢቡ ሰሎሞን ልብህን ስጠኝ እንዳለ ተረድተናል ። ይህ ብልህና መንፈሳዊ ደራሲ ገና በወጣትነት ዘመን ያለውን አዲስ ልብ ትኩስ ኃይልና ጉልበት ለእግዚአብሔር ሰጠ ይኸውም መስዋዕት በሚሠዋበት በገባኦን አንድሺህ የሚቃጠል መሥዋዕት ለፈጣሪው አቅርቦ ቃለ እግዚአብሔር ሌሊት በራዕይ ተገልጾ ምን እንድሰጥህ ለምን አለው ወጣቱ ሰሎሞንም አባቴ ዳዊት በእውነት በልብ ቅንነት ከአንተ ጋር በመሄዱ ታላቅ ቸርነት አድርገህለታል ዛሬም እኔን አገልጋይህን በአባቴ በዳዊት ዙፋን ተከትኸኛል እኔም መውጫዬንና መግቢያዬን የማላውቅ ታናሽ ብላቴና ነኝ ። አገልጋይህም ያለው አንተ በመረጥከው ሕዝብ ስለብዛቱም ይቆጠርና ይመጠን በማይቻል በታላቅ ሕዝብ መካከል ነው ስለዚህ በሕዝቡ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ መልካሙንና ክፉውንም ይለይ ዘንድ ለአገልጋይህ አስተዋይ ልብ ስጠው አለዚያማ በዚያ በታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል ።

ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር ማደሪያና ዙፋን እንዲሆን ልቡን ስለሰጠው እግዚአብሔርም ልመናው ስላስደሰተው ፍርድን ትለይ ዘንድ ለራስህ ማስተዋልን ለመንህ እንጂ ብልጽግናን ስጠኝ ጠላቴን አጥፋልኝ መንግሥቴን አብዛልኝ ብለህ ስላልመንኸ እንደ ቃልህ አድርጌልሃለሁ እነሆ ማንም የሚመስልህ ከአንተ በፊት እንደሌለ ከአንተም በኋላ እንዳይነሳ አድርጌ ጥበበኛና አስተዋይ ልቦና ሰጥቼሐለሁ ሲል በራዕይ አሳየው" አንደኛ ነገሥት ምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፬ - ፲፪ ፡

ሰሎሞንም አስተዋይና ቅን ልብ በማግኘቱ አስደናቂ ሥራ ሊሠራ ቻለ ጠላቶቹም ተገዙለት በፀጋም ላይ ፀጋ ስለተጨመረለት ሀብቱንና ንብረቱን ብቻ ሳይሆን ጉልበቱንም ላቡንም ድካሙንም ጭምር አፍሶ ስሙ የሚመሰገንበት ክብሩ ግርማውና ኃይሉ የሚገለጥበት አምልኮቱ የሚታወቅበት ማደሪያውና መኖሪያው የሚሆን በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ሠርቶ ለእግዚአብሔር አስረከበ ። እግዚአብሔር አምላክም በዚህ ቤተ መቅደስ እንደሚያድርና የለመኑ ሁሉ ለጸሎቱ መልስ እንደሚያገኝ ቃል ኪዳን ሰጠው ።

በመጨረሻ ግን ሰሎሞን ይህን የመሰለ ሥራ ካከናወነ በኋላ የሰው ልጅ ጠባዩን ፍቅሩን እየለወጠ ወዳጁን ጠላት ማድረግ ልማዱ ስለሆነ እሱም ገና በወጣትነት ዘመን አዲስ የሆነውን ልቡን ቅዱስ ኃይሉንና ጉልበቱን ሰጥቶ ያገለግለውና የመጀመሪያ ወዳጁና አምላኩ የሆነውን እግዚአብሔርን ጋሻ ከማድረጉም ሌላ የሠጠውን ልቡን ነጥቆ ለፈርኦን ልጅና ለሌሎችም ለእንግዳ ሴቶች ልቡን ሰጠ በፍቅራቸውም ስለተማረከ ባህላቸውንና ልማዳቸውን እያከበረ ወደ እነሡ በሐሣቡም በተግባሩም አዘነበለ በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ በወጣትነቱ ወራት እግዚአብሔርን ይከተል የነበረው ሰሎሞን በሽምግልናው ጊዜ ሌሎች አማልክት ይከተል ዘንድ በፍቅራቸው ሳቡት ስለዚህ የሲዶናውያንን አምላክ አስታሮትን አሞናውያንንም ርኩሡት ሞሎክን ተከተለ ።

ለነዚህም ጣኦት በኢየሩሳሌም መስገጃ ሥራ ለአማልክቶቹ መስዋዕት የሚሠሩና እጣን የሚያጥኑ ካህናትን አቋቋመ ይኸውም ሴቶቹን ለማስደሰት ሲል ነው ። ሁለት ጊዜ በራእይ ተገልጾ ያነጋገረውም እግዚአብሔርም ይህንን በማየት ተቆጥቶ ሥርዓቴንና ቃል ኪዳኔን አልጠበክምና መንግሥትህን ቀዳድጄ ለሁለት እከፍለዋለሁ ሲል ነገረው አንደኛ ነገሥት ምዕራፍ ፲፩ ቁጥር ፩ - ፲፪ ሰሎሞንም ለእግዚአብሔር የሰጠውን ልብ ወስዶ ለሴቶችና ለጣኦት በመስጠቱ ይህን የመሰለ መጥፎ ቅጣት እንደተቀጣ ተረድተናል ።

በዘመናችንም ቢሆን አንዳንድ አማኞች በአካሄዳቸውም ሆነ በምግባራቸው እንዲሁም በመጀመሪያ ጊዜ ልባቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት ጠቢቡ ሰሎሞንን ይመስላሉ ይኸውም በኋላ የገንዘብ አስተዋጽኦ አድርገው ቃሉን ሰምተው ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ ይህ መልካም ነበር እንደገና ተመልሰው ለእግዚአብሔር የሰጡትን ልባቸውን ለልዩ ልዩ ሚርት ለመስጠት እራሣቸው ተማርከው ሌላውንም ለማሳሳት በየዓመቱ የሚመጣው የዘመን መለወጫ በአል ለእኛም ሆነ ለቤተሰቦቻችን ጉንፋኑን ተላላፊውን በሽታ ይዞብን ስለሚመጣ አዲሱ ዘመን ጤና እንዲሰጠን የሰላም የሀብትና የእድሜ ዘመን እንዲሆንልን የሠራነው እንዲባረ



www.ethiopianorthodox.org

ክልንና እንዲበረክትልን መልክ ያለው በግና ዶሮ አርደን አዲሱን ዓመት መቀበል አለብን ይላሉ። አንዳንድ ሴቶችም በበኩላቸው መርከት ገበያ ገዝተው ያመጡትን ጠጠር መሳይ ጨሌያቸውን ከሙዳያቸው አውጥተው የጨሌ ልብሳቸውን ለብሰው ለብዙ ቀን የሚያበቃቸውን ገብስ ከከተው ትንጨ ቀቅለው በብዛት ቡና እያፈሉና ቅቤ እራሳቸውን እየተቀቡ ሌላውንም እየቀቡ ሀብትና ንብረታቸውን ማበላሸታቸው አልበቃ ብሎ ከአልጋቸው ወርደው ለሰስት ቀን ያህል መሬት ላይ ተኝተው ጨሌያቸው ከአዲሱ ዓመት ጋር እንድታስማማቸው ለነሡም ለልጆቻቸውም ጤና እና እድሜም ከበጋ ጋር እንድትሰጣቸው ሲለማመኑ ይሠነብታሉ ።

ይህን የመሰለውን መጥፎ ተግባር አማኝ ሊያደርገውና ሊፈጽመው የማይገባ ሥራ በመሆኑ መጀመሪያ ለእግዚአብሔር የሰጡትን ልብ እንደገና መልሶ ለጨሌና ለሰይጣን መስጠት ታላቅ ስህተት ነው ። ይሁን እንጂ አሮጌው ዘመን አልፎ አዲስ ዘመንን የምንለውጥበት የጨለማው ዘመን ሂዶ ጎህ ቀዶ ብርሃን መርጠን የምንተካበትና ከአዲስ ዘመን ጋር በሥራ የምንገናኝበት መሆኑን ልናውቀው ይገባል ። ይኸውም ሁላችንም በአዲሱ ዓመት የግል ሕይወታችንን መርምረን ከወጪያችንና ከገቢያችን ጋር የሚመጣጠን እቅድና መርሃ ግብር የምንነድፍበት ሲሆን ያለፈው ዓመት ክንዋኔያችንን በትዝታ ቃኝተን ደካማና ጠንካራ ጐን መርምረን አዲሱን ዓመት የተሻለ ሥራ የምንሠራበት ልባችንን የምናድስበትና መንፈሳችንን የምናጠናክርበት ነው እንጂ ለመጥፎ ባህል የምንበረከክበት ዓመት አይደለም። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሠጠነውን ልብ ለሌላ መስጠት እንደማይገባን ተረድተን አዲስ ሕይወትና አዲስ መንፈስ እንድናገኝ በአዲሱ ዓመት አዲስ ሥራ እንሥራ ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ዘመነ ሐዲስ

ከዕለተ እሑድ ጀምረው የተፈጠሩ ዕለታት ደጋግመው ራሳቸውን በመደመር ከሣምንት ወደ ወራት ከወራትም ወደ ወቅትና ዓመት ተጠቃለው እየተቆጠሩ የሰው ዘር ሕልውና ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ዘመናትን አስቈጥረዋል ።

ዘርአ ስብዕ በተለያየ መሠረታዊ አመለካከት ዘመን መቁጠር የጀመረበት ጊዜና ወቅት እንደየሀገሩ ባሕል ቢለያይም ቅሉ በዓመታቱ መፈራረቂያ ወር ወይም መለዋወጫ ወቅት ከሁለቱም ጠረፍ መካከል ሁኖ ወደ ኋላ የቀረውን ዓመት አሮጌ ሲል ወደፊት የሚያያዘውን ብሩህ የተስፋ ወቅት ደግሞ አዲስ ዓመት አዲስ ዘመን ብሎ መጠራቱ የተለመደ ነው ።

ዕለታትን በቀመራቸው ሦስት መቶ ስልሣ አምስት ቀኖች ሲሞሉ ዓመት የሚለውን ስያሜ የሚላበሱትም በዚሁ አጋጣሚ መሆኑ ይፋ ሆኖ ይታያል ዓመት የምንለው የዕለታት ቀመር የሦስት መቶ ስልሣ አምስት ቀናት ድምር ይሁን እንጂ በውስጡ አራት ወቅቶችንና አሥራ ሁለት ወራትን በአንድነት አካቶ ይዟል። እንግዲህ በዚህ አቆጣጠር የዓመታት ብዛት እየጨመረ ሂዶ ከመቶ በላይ በሚሆንበት ጊዜ በታሪክ ጸሐፊዎች ዘንድ ዘመን ተብሎ ይጠራል ።

የታሪክ ሰዎች መቶውን ዓመት አንድ ዘመን ሲሉ ከዚያ በላይ የሆነ ቁጥር ያለውን ደግሞ ሁለተኛው መቶ ክፍለዘመን ወዘተ በማለት አጠቃለው ይጠሩታል ። በዚህ ሁኔታ የታሪክ ሰዎች ዘመን ብለው የሰየሙት በመቶ ብዛት የሚቆጠር ዓመታት እንደሆነ ከተረዳን በቅዱሳት መጽሐፍትና መንፈሳውያን ሊቃውንት አነጋገር ደግሞ ለየት ያለ ትርጉም ለዘመን እንደተሰጠው እንመለከታለን

ምንም እንኳን መቶና ከመቶ በላይ ላሉ ዓመታትም ዘመንን የሚጠቀሙ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ደግሞ ለወቅቱና ለአነስተኛ ዓመታት ዘመን እያሉ እንደሚጽፉ ስናይ ከታሪክ ምሑራን ጋር ያለው የቋንቋ ምንዛሬ ለአንባቢያን ግራ የሚያገባ ይሆን ይሆናል።

ለምሳሌ የታሪክ ምሑራን አባባል አሁን ያለንበት ክፍለ ዘመን ሃያኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን አትዘንጋ ብንባል ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ዓመተ ምሕረት ላይ መሆናችንን ስንረዳ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን አባባል ደግሞ የአንድ ዘመን ድኅን አሂጀለሁ (ተምሬአለሁ) ብንል የተለየ ትርጉም ይሰጠናል ።

በመጻሕፍተ ቤተ ክርስቲያንም መ/ኩፋሌ ፴፱፡፲፱ ዮሴፍ የመቶ አሥር ዓመት ልጅ ሲሆን ሞተ ። በከነዓን አሥራ ሰባት አመት ኖረ። አሥር ዓመት ሲያገለግል ኖረ ። ሦስት ዘመን በግዞት ሰማንያ ዘመን ከንጉሥ በታች ሆኖ በግብፅ ሀገር ሁሉ ሲገዛ ኖረ ። ሲል ም·፲፪· ቁ· ፲፬ .. ከእባቡ ፊት ርቃ አንድ ዘመን ዘመናትም የዘመንም እኩሌታ ወደ እምትመገብበት ወደ ሥፍራዋ ወደ በርሃ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የትልቁ ንሥር ክንፎች ተሠጡትና ይላል።

አባባሉም ከሄሮድስ ፊት ሸሽታ በዘመኑ ሁሉ ወደ ምትጠበቅበት ምድረ ግብፅ በስደት ትሄድ ዘንድ ለእመቤታችን ንጽሐ ሥጋ ንጽሐ ነፍስ ተሠጣት በማለት የሚያስተረጉም ሲሆን ዘመን ያለውን ለመተርጐም የስደቷን ዓመታት እንጂ በመቶ የሚቆጠር ጊዜ አለመሆኑን እንረዳለን ።

ያም ሆነ ይህ በመሠረቱ ለዘመን መጀመሪያና መጨረሻ ስለሌለው አዲስና አሮጌም ሊኖረው አይችልም ። በጥንት ተፈጥሮ የተገኙት ዕለታት ተደምረው የሚሠጡት የመሽከርከር ውጤት እንጂ ሌላ የተጨመረ አዲስ የሚያሰኝ የፈጠራ ግኝት የለምና ነው ። ዘመኑን አዲስ የሚያሰኘው የእኛ ሥራ ሊሆን ይገባል ።

ለዚህም ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ከተናገሩት እጠቅሳለሁ ። የዘመን መጀመሪያና መጨረሻ ስለሌለው ዘመን ተለወጠ ለማለት አይቻልም ። የማይለወጠውን ዘመን ተለዋጭ የሚያደርገው የሰው ልጅ ታሪክ ነው ። ለምሳሌ ለኢትዮጵያ የጥንቱ ከዛሬው የዛሬው ከወደፊቱ የሚለየው የቀደሞው ዘመን የአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ተያይዘው የእኛ የወደፊት ኢትዮጵያ የምትወልዳቸው ኢትዮጵያውያን ዘመን በመሆኑ ነው ።

ሦስቱ ክፍላተ ዘመን የተለያዩ ቢሆኑም ባለቤቶቹ ኢትዮጵያውያን ጽኑ በሆነ በማይቆረጥና በማይበጠስ መንፈስ የተያያዙ ናቸው ያለፉት አባቶቻችን የኖሩት ለራሳቸው ብቻ አልነበረም ። ተግባራቸው ትርሳቸው ለእኛ ተርፎአል እኛም የምንኖረው ለራሳችን ብቻ አይደለም .. ብለዋል ፡

በዚህ አንፃር ለዘመኑ አዲሶች እኛ የዘመኑ ትውልዶች እንጂ ዘመኑ አዲስ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም ቀመሩን ጠብቆ ያለ ማሰለስ የሚመላለስ በመሆኑ በአዲስነታችን ሳንሠራበት ነገ ተሽከርክሮ እንዳይደርስብን ልንጠነቀቅ ይገባናልና ነው ። ዘመን ልንሠራበት እንጂ እንዲሠራብን አያስፈልግም በዘመንም የምንሠራው ሥራ የምንተልመው ትልምና በሃሳብም የምናቅደው ዕቅድ ሣይቀር ለትውልድ አልፎ የሚጠቅምና ሀገርን የሚያኮራ መሆን ይገባዋል።

ለማጠቃለል የአዲሱ ዓመት ሥራችን የሰውን ልጅ ጉልበት ከብዝበዛና ውጣ ውረድ ድካም በጥቂቱም እንኳን የሚያሣርፍ ፈጠራ ውጤት የምናሳይበት ዓመት እንዲሆን ያስፈልጋል ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ማይሆን ነውርና ዕድፍ እንደሌለው እንደበግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደተዋጃችሁ ታውቃላችሁ .. ብሎ እንዳስተማረን የዛገውን ያረጀውን የቂም በቀል ጉተራ አእምሮአችን በንስሐ መታደስና በአዲስ መንፈስ መሥራት ይጠበቅብናል የምሻው በአዲስ መንፈስ አዲስ ምድርና አዲስ ሰማይ ነውና ።

.. ጽድቅ የሚኖርባት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድርን እንደተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን ። ስለዚህ ወዳጆች ሆይ ይህን እየጠበቃችሁ ያለነውርና ያለነቀፋ ሁናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ ። ፪ኛ ጴጥ ፫ ፲፫ ይላል በዚሁ መሠረት ሁላችንም በአዲስ መንፈስ አዲስ ሥራ ለመሥራት እንነሣ ።

አባ ብርሃን መስቀል አየሁ

# አጥማቂው ባሕታዊ (ዮሐንስ መጥምቅ)

በተለያዩ ዘመናት ልዩ ልዩ ታላላቅ መንፈሳውያን አባቶች ተነሳስተዋል ፡ በዘመናቸውም ብዙ ታላላቅ ሥራዎች ተሠርተዋል ፡ ለምሳሌ ከዘመነ አበው አብርሃምን ፡ ከዘመነ መሣፍንት ሙሴን ፡ ከዘመነ ነቢያት እነኢሳይያስን እነ ኤርምያስን እነ ሕዝቅኤልንና የመሳሰሉትን ስናስታውስ ሥራቸው ከታላቅነታቸው ጋር ለረጅም ዘመናት እንደኖሩና የሚያበሩ መሆኑን ርእስ መጻሕፍት የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ፡ ከነዚህም አባቶች ቀጥሎ በሐዲስ ኪዳን መግቢያ ዋዜማ ላይ የተነሣው ዮሐንስ ነቢይ እንደታላላቆቹ አባቶች ነቢይ ነበር

የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች ፡ የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በነቢዩ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል .. ሉቃ· ም· ፩· ቁ· ፲፯

በዚህ ትንቢታዊ የምሥራች በእግዚአብሔር መልአክ በቅዱስ ገብርኤል አንደበት የተነገረለት የአማናዊው ካህን የዘካርያስ ልጅ አዋጅ ነጋሪ ሰባኬ ጥምቀት ፡ ነቢይ ፡ ካህን ፡ መምህር ወመገሥጽ ፡ መጥምቀ መለኮት የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ ነው ።

ቅዱስ ዮሐንስ ከዛሬ ፲፱፻፹፬ ዓ ም ቀደም ብሎ የነበረ ሲሆን አባቱ በመዘመሪያው በዳዊት ዘመን ለቤተ መቅደስ አገልግሎት በሰሞን ከተመደቡት ካህናት አንዱ ከነበረው አብያ ፩ኛ ዜና መዋ· ም· ፳፬· ቁ· ፲ ከተባለው ካህን ዘር የተወለደ እናቱ ደግሞ ከታላቁ ካህን ከአሮን ዘር የተወለደች ሁለቱም የእግዚአብሔርን





www.ethiopianorthodox.org

ትእዛዝና ሕግጋት በመጠበቅ ምንም ነቀፋ የሌለባቸው ፡ ዘወትር በቅድስና የሚኖሩ ጻድቃን ነበሩ ፡ ስማቸውም ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ይባል ነበር ፡ እነዚህም ሰዎች በዘመናቸው ልጅ ያልነበራቸው መካኖች በመሆናቸው እግዚአብሔርን ብቻ በማገልገልና ደጅ በመጥናት እስከ ዕርግና የደረሱ ለመሆናቸው ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ፡ ሉቃ· ም· ፩—፯

በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳሉ ካህኑ ዘካርያስ በሰሞን ተራው ከቤተ መቅደሱ ገብቶ ሲያገለግል መለአከ እግዚአብሔር ቅ/ገብኤል ከመሠዊያው ወይም ከመንበሩ በስተቀኝ እንደቆመ ተገልጾ ጸሎትህ በእግዚአብሔር ፊት ደርሶ ተሰምቶልሃል ፡ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃች ። ስሙንም ዮሐንስ ብለህ ትጠራዋለህ ፡ ዮሐንስ ማለት ፍጹም ደስታ ማለት ነው ፡ እርሱም በእምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል ብዙዎችንም ወደንስሐ ይጠራል .. ሉቃ.ም. ፩.ቁ. ፰ ፲፯ ብሎ በነገረው መሠረት ታላቁ ነቢይና አጥማቂ ባሕታዊ የተባለው ቅዱስ ዮሐንስ ተወልዶ ገና በሕፃንነቱ እናቱ ኤልሳቤጥ በሞት ስለተለየችው በበረሃ ወድቆ ከፍተኛ የብሕትወና መንፈስ በእግዚአብሔር ፈቃድ እንደኖረና በዚያም ልብሱ የግመል ጸጉር ምግቡም የበረሃ (የጋጃ) ማር እንደ ነበረ ሁላችንም የምናውቀው ነው ፡ ማቴ·ም·፫·፩—

ይህም እውነተኛ ባሕታዊ በሐ· ሥራ ም·፬ ቁ· ፲፱ እንደተገለጸው ለሰው ከመታዘዝ ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ እንደሚበልጥ ስለሚያምን

ሕዝበ እስራኤልን ወደ ንስሐ እየጠራ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና በዮርዳኖስ ወንዝ በእርሱ እጅ እንዲጠመቁ እንዲህ ይላቸው ነበር ፡ እንግዲህ ከሚመጣባችሁ መቅሥፍትና መከራ እንድታመልጡ ንስሐ ግቡ እኛ የአብርሃም ዘር ነን ማለት አያዋጣችሁም ። መልካምና በጎ ነገሮችን ማድረግ ይሻላችኋል ። እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ከእኔ ቀጥሎ የሚመጣው ፡ እኔ ከደካማነቴ የተነሣ የጫማውን ማሠሪያ ጠፍር (ገመድ) ለመፍታት አቅም የሌለኝ በኃይሉና በችሎታው የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ ፡ የእግዚአብሔር በግ ነው ፡

እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳት ያጠምቃችኋል ማቴ.ም.፫ ቁ. ፯ ፲፩ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደእርሱ መጥቶ ሳይገ ቀውና ሳያቃልለው በእጁ ስለተጠመቀ <u>መጥምቀ መለኮት</u> ተባለ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀድሞ በማስተማሩና በመስበኩም አዋጅ ነጋሪ የሚባል ሥያሜን አገኘ ሴቶች ከወለዱዋቸው መካከል ከርሱ በፊትም ሆነ በኋላ የሚበልጠው እንደሌለ የተነገረለት ይህ ዮሐንስ ነው ፡ ቅዱስ ዮሐንስ የዘመኑን ንጉሥ ሄሮድስን ሳይፈራ (ሳያፍር) ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን ለራሱ ሚስት አድርጎ ወስዷት ስለነበረ ቆራጡና እውነተኛው ባሕታዊ ዮሐንስ ··· አንተ የወንድምህን ሚስት ማግባት አይገባህም ·· ብሎ በድፍረት ስለገሠጸው ይዛችሁ አምጡና እሠሩት ብሎ አገልጋዮቹን አዞ በወህኒ ቤት እንዲታሠር ፈርዶበት በወህኒ ቤት እንዳለ የሄሮድስ የልደት በዓል ደርሶ ሲከበር ሹማምንቱና ታላላቆቹ ባሉበት ሲበላና ሲጠጣ ሲዘፈንና ሲጨፈር ለሄሮድያዳ ጥሩ አጋጣሚ ስለነበረ ሴት ልጇን ወደ በዓሉ ላከቻት ፡ በዚህ ጊዜ ልጅቷም ሄሮድስንና ተከታዮቹን በዘፈኗና በጭፈረዋ ደስ ስላሰኘቻቸው ሄሮድስ ·· የፈለግሽውን ነገር በዛሬው ዕለት ብትጠይቂኝ እፈጽምልሻለሁ ብሎ በመሐላ ቃል ሲገባላት እሷም ለበጎ ሳይሆን ለክፉ አስቀድማ ተዘጋጅታ ስለነበረ ·· የዮሐንስን ራስ አንገቱን አስቆርጠህ ስጠኝ ··አለችው· ሄሮድስም አሽከሮቹን ልኮ በወህኒ ቤት እያለ መስከረም ፪ ቀን አንገቱን በሰይፍ አስቆርጦ እንደሰጣት ቅዱስ ዮሐንስም በዚሁ ዕለት ምድራዊት ሕይወቱን እንደፈጸመ ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ማር· ም·፮·ቁ ፲፬—፳፰ በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያናችን በየዓመቱ መስከረም ፪ ቀን በዓለ ዕረፍቱን በከፍተኛ ድምቀት ታከብራለች እንግዲህ እውነተኛ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ልጆች የሆንን በዓሉን ስናከብር ቅዱስ ዮሐንስ እንዳዘዘን ንስሐ እየገባንና በትዕቢት ተራራ የሆነውን ልባችንን ዝቅ በማድረግ ተስፋ በመቁረጥ ዝቅ ያለውንም ሕሊናችንን ከፍ እያደረግን በእማላጅነቱ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ እንዲያስችለን አምላካችንን እንለምነው ።

ቀሲስ ምሕረት ዘውዱ



## ዜና ሊቃውንት

# የመሪጌታ አስፋው መኮንን የሕይወት ታሪክ በአጭሩ

### ከብፁዕ አቡነ ቄርሎስ የዋግና የላስታ የየጁ ጳጳስ

በዛሬው የሊቃውንት ዓምዳችን የምናቀርበው በሕየወተ ሥጋ እያስተማሩ ከሚገኙት ሊቃውንት መካከል የመሪጌታ አስፋው መኮንን የሕይወት ታሪክን በአጭሩ ነው ። መሪጌታ አስፋው መኮንን ከአባታቸው ከአቶ መኮንንና ከእናታቸው ····በወሎ ሀ/ስብከት በራያና ቆቦ አውራጃ ደሐባ ማርያም ከምትባል ደብር በ፲፰፻፺፪ ዓ.ም. ተወለዱ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ወደ ትምህርት ቤት ገብተው ፊደል ቆጥረው ንባብ አንብበው ዳዊት ከደገሙ በኋላ በየትምህርት ቤቶች እየዞሩ ከተለያዩ መምህራን ፀዋተወ ዜማ ፡ ቅኔ ከእነ አገባቡ ከተማሩ በኋላ አቋቋም ዝማሬ መዋሥዕት ቅዳሴ ተምረዋል በ1923 ዓ·ም· ወደ ጎንደር ሀገረ ስብከት ሔደው ጋይንት አውራጃ ከምትገኘው ቤተልሔም ያን ጊዜ ወንበሩን ይዘው ከነበሩት መሪጌታ መርሻ ቀደም ሲል ከተለያዩ መምህራን ተምረውት የነበረውን ድጓ ከልሰው በሚገባ በማወቅ ተመርቀው የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

በድጓ መምህርነት ከተመረቁ ጀምሮ 55 ዓመት ሙሉ ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው በንታትና በትጋት በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አሠልጥነው ለቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

መሪጌታ አስፋው መኮንን 3 ወንዶች 8 ሴቶች ልጆች አሏቸው ወንዶች ልጆቻቸውን በማስተማር ከመምህርነት ደረጃ እንዲደርሱ አድርገዋቸዋል ለማስረጃ ያህል 1ኛው መሪጌታ በላይ አስፋው ይባላል የአቋቋም መምህር ነው 2ኛው መሪጌታ ፍቅረ ማር


መሪጌታ አስፋው መኮንን በማስተማር ላይ እንዳሉ

ያም መኮንን ይባላል የዜማ መምህር ነው 3ኛው ም ልጃቸው ቅዳሴ ያስተምራል ሴቶች ልጆቻቸውም ኑሯቸው በገጠር ስለሆነ የመማር ዕድል ባይገጥማቸውም ሁሉም በትዳር ላይ መሆናቸው ታውቋል ይህም የሚያስረዳው የወላጆቹን ቁም ነገረኛነት ነው ሊቁ ከዚህ ዓልፈው የልጅ ልጆቻቸውንም በማስተማር ላይ ይገኛሉ በአሁኑ ጊዜ ዕድሜያቸው ፹፰ (ሰማንያ ስምንት) ቢሆኑም የማስተማር ተግባራቸውን አላቋረጡም ካስተማሩአቸውም መምህራን ስባቱ ወንበር ተክለው ጉባኤ አስፍተው በማስተማር ላይ ይገኛሉ በጣም የሚስደንቀውና የሚያስገርመው በዚህ ዕድሜያቸው አቀበቱን ወጥተው ቁልቁለቱን ወርደው ቤተ ክርስቲያንን ከማገልገላቸውም ሌላ ራሳቸውንም በራሳቸው እየረዱ መኖራቸው ነው ።

አሁንም ቢሆን በርከት ያሉ ተማሮች አሏቸው እነርሱም ዙሪያውን ከበው እንደንብ እንዱ ዜማውን ሌላው አቋቋሙን ዝቀተኛው ደግሞ ዳዊቱንና ንባቡን ሲያነበንበው እጅግ የሚያስገርም ሆኖ ተመልክተነዋል ። ሊቁ የቀለም ባለሙያ ብቻ ሳይሆኑ ሥልጣነ ክህነትም ያላቸው በመሆናቸው በቅዳሴም በኩል አገልግሎት የሚያበረክቱ በሁለመናው የተሟላ ሞያ ያላቸው ናቸው ።



www.ethiopianorthodox.org

ከእኒህ ሊቅ ሊወሰድ የሚገባው ታላቅ ቁም ነገር አለ ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸጋ ዘነሣዕክሙ በጸጋ ሀቡ ዋጋ ሳትሰጡ የተማራችሁትን ዋጋ ሳትቀበሉ አስተምሩ ያለውን ቃል ብመከተል ይህንን ያህል ዘመን ከማንም ዋጋ ሳይጠይቁ ዋጋዬን ፈጣሪዬ ይሰጠናኛል በማለት ሲያስተምሩ መኖራቸውና አሁንም በማስተማር ላይ መገኘታቸው ነው በአሁኑም ጊዜ የልጅ ልጆቻቸው ንባብና ዳዊት ወዳሴ ማርያም በመማር ላይ የሚገኙ መሆናቸውን መሪጌታ አስፋው መኮንን አስረድተውናል :

“ሠናይ ዕፅ ሠናየ ፍሬ ይፈሪ” መልካም እንጨት መልካም ፍሬን የፈራል እንደተባለው እንደነአብርሃምና እንደነኢዮብ ከእነ ልጆቻቸው እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ የሚገኙት መሪጌታ አስፋው መኮንን ለተከታይ ትውልድ በአርአያነታቸው ሊጠቀሱ የሚገባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል ። ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት ለመሆን የበቃው የእግዚአብሔር አገልጋይ ከሆነው ከዘካርያስ በመገኘቱ ነው ታላቁ ጻድቅ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም የካህኑ የፀጋ ዘአብ ልጅ በመሆናቸው ነው ከታላቅ ክብር ለመድረስ የበቁት :

የካህን ልጅ ካህን አልሆንም እያለ በሚኮበልልበት በአሁኑ ጊዜ መሪጌታ አስፋው መኮንን ልጆቻቸውን እያስተማሩ በማሳደግ የእርሳቸውን ሞያ ይዘው ቤተ ክርስቲያንን እንዲያገለግሉ በማድረጋቸው ሊመሰገኑ የሚገባቸው ናቸው :

የተማረው ሁሉ እያስተማረ ልጆቹን በእግሩ እየተካ ቢያልፍ ቤተ ክርስቲያናችን የወላድ መካን ከመሆን ትድናለች ይህንንም ስንል ያልተማረው ምእመን ልጆቹን መንፈሳዊ ትምህርትን እያስተምር ማለታችን አይደለም ለቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት የሚቀርቡ ካህናት መሆናቸውን በመመልከት ከምእመናን በበለጠ በማሰብ ልጆቻቸውን አስተመረው እነርሱን አስመስለውና አሳክለው ለቤተ ክርስቲያን እንዲያበረክቱ ለማሳሰብ ነው ።

# ትእግሥት እንደ ኢዮብ

በሰዎች የህልውና ዘመናት ውስጥ መልካም ሥነ ምግባርን ከመሠረታዊ ታሪክ ጋር ቀርጾ ለማለፍ ሰዎች ከሚችሉባቸው ቁም ነገሮች መካከል ትዕግሥት ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል ።

በመሆኑም በሕይወት ዘመናቸው ትዕግሥትን ተጐናጽፈው ያለፉትን የሃይማኖት አባቶችን ስናስብ ብዙዎች ናቸው በመልካም ሥነ ምግባር የጐለበተውን የእነዚህን አባቶች ታሪክ ስንመለከት በትዕግሥታቸው የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛላቸው መሆኑን እንረዳለን ።

በብዝሐ ትዕግሥት የእግዚአብሔርን ጸጋ ከታደሉ ሰዎች መካከል አንዱ ጻድቁ ኢዮብ ነው ከቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ በራሱ በኢዮብ መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ እንደተመዘገበው ኢዮብ የሚኖርበት አገር ኦፅ ይባላል ይህ ሰው ፍጹም ቅን ፡ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፉ ነገር ሁሉ የራቀ ነበር ። ለዚህ ጻድቅ ሰው በብዛት የተትረፈረፈ ሀብት ነበረው በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በጐችና ግመሎች ነበሩት ሰብአት ወንዶችና ሶስት ሴቶች ልጆች ነበሩት ጻድቁ ኢዮብ የወለዳቸው ልጆች ከእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ እንዳይወጡ ዘወትር ይመክራቸው ነበር ። እነርሱም የአባታቸውን ትዕዛዝና ምክር በመቀበል የኢዮብ ልጆች እግዚአብሔርን ያከብሩና ትዕዛዙንም ይጠብቁ ነበር በመልክም ሆነ በሥነ ምግባር የተወደዱ ነበሩ ።

ከጊዜ በኋላ ግን በሰይጣን ተንኮል ምክንያት ለጻድቁ ኢዮብ የነበረው ሀብት ሁሉ ጠፋ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹም ሁሉም ሞቱ ለኢዮብ ምንም ነገር የቀረው አልነበረም ከዚህም የበለጠ አሰቃቂ ሥቃይ የኢዮብ አካል በሙሉ በቁስል ህመም ተይዞ ነበር ሆኖም ይህን የመሰለ አስከፊ ሥቃይ በጻድቁ ኢዮብ ላይ ቢፈራረቅበትም እርሱ ከአለው የእግዚአብሔር አምልኮት ፈቀቅ አላለም ።

ይልቁንም ... እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሣ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን ሲል አመሰገነ እንጂ ጻድቁ ኢዮብ በደረሰበት አስከፊ ችግር ምክንያት ሚስቱና ጓደኞቹ ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጣላና ስንፍናን እንዲናገር ሲገፋፉት የእነሱን ሥህተት ከመንቀፍ በቀር የደረሰበትን መከራ ሁሉ ታግሶ እግዚአብሔርን ከማመስገን አልተቆጠበም ።

በሰይጣን ተንኮል የደረሰበትን አስከፊ ሥቃይ በመታገሥ ጻድቁ ኢዮብ ብዙ ጊዜ ቆየ በትዕግሥትና በመልካም ሥነ ምግባር ለሚኖሩ ሰዎች ዋጋ ከፋይ እግዚአብሔር አምላክ ጻድቁ ኢዮብን አልረሳውም ነበር ጻድቁ ኢዮብ ከብዙ ሀብቱና ከልጆቹ ተለይቶ ራሱም በአስከፊ የቁስል ህመም ሳለ እግዚአብሔር አምላክ ወደ ኢዮብ ተመለከተ ከቁስሉም ፈወሰው ። የነበረውንም ሀብት ከአለፈው በእጥፍ መለሰለት ደግሞ ሰባት ወንዶችና ሰባት ሴቶች ልጆች ሆኑለት በሰይጣን ቅንዓት ምክንያት በጻድቁ ኢዮብ ላይ ለተወሰኑ ጊዜያት ችግርና መከራ ቢፈራረቁበትም በትዕግሥቱና በአለው የእግዚአብሔር ፍቅር ከነበረበት አስከፊ ሥቃይ ተላቆ በሰላምና በደስታ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ ኖሮአል ።

ጻድቁ ኢዮብ ከምድራዊውም ሕይወቱ ፍጻሜ በኋላ የእግዚአብሔር መንግሥት ባለቤት እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት እንረዳለን ።

የትዕግሥት ባለቤት እግዚአብሔር አምላክ እንደ ጻድቁ ኢዮብ ትዕግሥትን ተላብሰውና ተጎናጽፈው የሚኖሩትን ሰዎች የሚያጽናና የሚረዳ መሆኑን ሲገልጽ “.. …ትዕግሥቱን እስከ መጨረሻው ድረስ ያዘወተረ እርሱ ይድናል ። ....” ሲል በትምህርተ ወንጌሉ ላይ ለሰዎች የትዕግሥትን ጠቃሚነት አስተምሯል ። በዚህም ጌታ በአስተማረው የወንጌል ትምህርት ተጠቅመው ትዕግሥትን ገንዘብ ያደረጉ አባቶች ብዙዎች ናቸው በተለይም አባቶቻችን ሐዋርያት ጻድቃንና ሰማዕታት በትዕግሥት የተፈተነ ሕይወት ነበራቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እነዚህ የትህግሥት ብዛት በዕብራውያን መልዕክቱ ላይ በምዕራፍ ፲፩ቍ· ፴፰ በሚገባ አድርጐ በዝርዝር የገለጸውን ማንበብና መረዳቱ ይበቃል።

ቅዱስ ያዕቆብ ትዕግሥት ያላቸው ሰዎች ከእግዚአብሔር ዋጋ ያላቸው መሆኑን ሲገልጽ “....በትዕግሥት የሚጸና የተባረከ ነው ከፈተና በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወት አክሊል ይቀበላልና ...” ያዕቆብ ፩·፲፪ — ፲፬ ሲል ትዕግሥት ያላቸው ሰዎች ከምድራዊው ዋጋ የበለጠ ሰማያዊ ዋጋ እንዳላቸው በሚገባ አድርጐ አስረድቷል።

እንግዲህ እያንዳንዳችን የትዕግሥትን ጠቃሚነት በመገንዘብ በትዕግሥት ለነበሩት አባቶቻችን እግዚአብሔር የሰጣቸውን ዋጋ በማየትና ትዕግሥት ለሰዎች ሁሉ የሰላም መሥረት መሆኑን በመረዳት ለምን ጊዜም ትዕግሥትን ገንዘብ እናድርግ ያለ ትዕግሥት የተሠራና የሚሠራ ውጤት ያለው ሥራና የሰላም ኑሮ የለምና .... ትዕግሥትን ገንዘብ አድርጎ የእግዚአብሔር ፀጋ ባለቤት ለመሆን ያበቃን ጻድቁ ኢዮብን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ መስከረም ፩ ቀን ታከብራለች ።

መ/ኤፍሬም በየነ

# የጥንት ወንጀለኞች መቅጫ የዛሬው መዳኛ

ዓለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ የሰው ልጆች በምድር ላይ መብዛት ከጀመሩበት ጊዜ እንሥቶ እስካለንበት ዘመን ድረስ ልዩ ልዩ ወንጀል ለፈጸሙና ለሚፈጽሙ ሰዎች የተለያየ የቅጣት መፈጸሚያ የተዘጋጀ መሣሪያ እንደነበረ ታሪክ ያወሳናል ።

ከእነዚህም መሣሪያዎች አንዱ “መስቀል ነበር” መስቀል አንዱ ግንድ ቀጥ ብሎ ሲቆም ሌላው መስሉ (አክሉ) ግንድ ደግሞ ከፍ ብሎ አግድም በገመድ ወይም በምሥማር የሚያያዝ ነው :

በመሠረቱ መስቀል የመከራ : የሥቃይና የበደል መሣሪያ ነው : መስቀል ከልደተ ክርስቶስ በፊት የሚያነሣውና የሚያስታውሰው ሁሉ እጅግ ይሰቀቅ ነበር ይልቁንም እሥራኤላውያን በድሮ ጊዜ መስቀል እንደ ወንጀለኛ ሕግ መቅጫ አድርገው ይጠቀሙበት የነበረ መሣሪያ ነበር ።

ከዚህም የተነሣ በዚያን ጊዜ የነበሩት ሰዎች ሁሉ አመለካከታቸው በመስቀል ተሰቅሎ የሞተም ሆነ የሚሞት ሰው ፍጹም ዝቅተኛና ከሁሉ በታች የሆነ ሰው ነው ብለው ያምኑበት ነበር በዕንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ሰው በሰውም በእግዚአብሔርም የተረገመ ነው በሚለው ሀሳብ ከመጽናታቸውም በላይ በሕግ መጽሐፋቸው” ማናቸውም ሰው ለሞት የሚያደርሰውን ኃጢአት ቢሠራ ሞት ቢፈረድበት አንተው በዕንጨት ላይ ብትሰቅለው ሬሣው በዕንጨት ላይ አይደር ነገር ግን በዚያን ቀን ቅበረው በዕንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ ከእግዚአብሔር ተረግሞአልና” ይላል (ዘዳ፳፩ :፳፪)

ይህ የመከራ የሥቃይ : የውርደትና የጉስቁልና ምልክት የሆነው መሣሪያ በሰዎች ጫንቃ ላይ ተጭኖ ፭ሺ፭፻፺፱ ዓመታት ያህል ሲኖር አንድም ስንኳ የሚያሻሽለውና የሚያስቀረው ሰው አልተገኘም ነበር ።

ይሁን እንጂ ይህ የመከራና የስቃይ ቀንበር ለ፭ ሺህ ፭፻ (አምስት ሺህ አምስት መቶ) ዘመን





www.ethiopianorthodox.org

በሰዎች ላይ ሲፈጸም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ርጉማን ተብለው የሐሳርና የውርደት ስም ከመውረሳቸውም በላይ በመስቀል ተሰቅለው በሚሞቱ በአዳምና ሔዋን ልጆች ቦታ ተተክቶ ተሰቅሎ ፡ በሞቱ ሞትን ፡ አጥፍቶ ነጻ እንደሚያወጣቸው በየጊዜው የተነሡት ነቢያት ተናግረውለታል ።

በተለይም ነቢዩ ኢሳይያስ "በእውነት ድዌአችንን ተቀበለ ሕመማችንንም ተሸክሞአል እኛ ግን እንደተመታ በእግዚአብሔርም እንደተቀሠፈ እንደተቸገረም ቆጠርነው እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ ስለበደላችንም ደቀቀ የደህንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበር በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን" ብሏል (ኢሳ ፶፫፡፬፡)

ጊዜ ሲደርስ አምባ ይፈርስ እንዲሉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንቢቱ መሠረት በሥጋ ሰብእ ተገልጾ በሚያስተምርበት ጊዜ "ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም ሊሰቀል ይገባዋል" ሲል ተናግሯል ።

ዲያብሎስ በረቀቀ ተንኰሉ በግዙፍ ዕባብ አድሮ አዳምንና ዘሩን ከኀጢአት አዘቅት እንደጣላቸው ሁሉ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስም በግዙፍ ሥጋ ሰብእ ተዋሕዶ በመስቀል ተሰቅሎ የዲያብሎስን ተንኰል በረቀቀ ምሥጢር ደምስሶ አዳምን ከነዘሮቹ ነፃ አውጥቶቸዋል ፡ (ዘኁል ፳፩ ፰፡፱ ዮሐ ፲፬)

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መስቀል የመከራ የውርደትና የተስቁልና መጠሪያ መሆኑ ቀርቶ የሰላም የደስታ የነፃነት ፡ የአንድነትና የፍቅር መጠሪያ ሆኖአል ። ከዚህም በላይ የአጋንንት አኩያን ድል መንሻ ነው ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "በዕንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጀን" ብሎአል በእርግጥ ከዚህ አስደንጋጭ አስፈሪና አስጨናቂ ፍርድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ሞትን ደምስሶ ነፃ ስላወጣን ወደር የማይገኝለት ደስታ ይሰማናል (ገላ ፫—፲3)

መስቀል የፍቅር ፡ የሰላምና የድል መጠሪያ መሆኑን ሐዋርያት በየመልእክቶቻቸው ዘግበዋል ፡ ክርስቶስ በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል ለብዙ ዘመናት አለያይቶ የኖረውን የጥል ግድግዳ በመስቀሉ አፈራርሶ የጣለ ርቀው ለነበሩ ሰላምን ቀርበው ለነበሩትም ደግሞ የምስራችን አብስሮ የሰበከበት ነው ።

መስቀል ልዑል እግዚአብሔር ሰው የሆነበትን ያከናወነበት ፡ ለዓለም ሁሉ ነፃነትን የሰበከበት ክቡርና ቅዱስ ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔር ኃይል ነው ። በዚህም መሠረት ነው ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት ፡ እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ በማለት በመስቀል ስለተገኘው ጸጋ በሠፊው የጻፈው" (ገላ ፮—፲፬)

በዚሁ ትምህርት መሠረት መስቀል በሀገራችን በኢትዮጵያ ትልቅ ክብር አለው "ኢትዮጵያውያን ስለመስቀል ያላቸው ፍቅር እጅግ የላቀ ነው" ሴቶችም ሆኑ ወንዶች በእጃቸው በግምባራቸው ፡ በአንገታቸውና በባታቸው ሁሉ በንቅሳት መልክ ይስሉታል" ከዚህ ሌላ በቀሚሳቸውና በጋቢያቸው እየጠለፉ ያጌጡበታል ፡ በልዩ ልዩ የቤት ዕቃዎቻቸው በየቤታቸው ግድግዳና በመጣሪያዎቻቸው ሁሉ የመስቀል ምልክት ያደርጉበታል ።

ይሁን እንጂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል አይሁድ ተአምራት ሲሠራ አይተው ምድር ቆፍረው ቀብረው ለብዙ ዘመናት አቆዩት ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በንግሥት ዕሌኒ አድሮ መስቀሉ ተቆፍሮ ከወጣ በኋላ ድውይ እየፈወሰ ሙት እያነሣ ለምፅ እያነፃ አምላካዊ ኃይል በማሳየቱ የክርስትና እምነት ቀደምትነት ያላቸው አገሮች በየግማዱ ተከፋፍለው በየሀገራቸው አስቀምጠውታል ።

ዕሌኒ መስቀሉን ለማግኘት ደመራ አቀጣጥላ ቁፋሮ የጀመረችበት ዕለት መስከረም ፲፯ ቀን በመሆኑና መስቀሉ የተገኘው ወይም የወጣው መጋቢት ፲ ቀን ስለሆነ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ሁለቱንም ዕለታት ስታከብራቸው ትኖራለች ።

መስቀል እንደ አይሁድ የሚንቁትን ሰዎች ያጠፋቸዋል እንደ እሌኒና እንደ ልጅዋ እንደ ቆስጠንጢኖስ ለሚያከብሩትና የሚተማመኑት ግን ተስፋቸውና መመኪያቸው ነው ። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "የመስቀሉ ኃይል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና" ያለው (፩ኛ ቆሮ ፩፡ ፲፰)

መስቀሉ በንግሥት ዕሌኒ ከፍተኛ ጥረት ከተገኘ በኋላ በዚያን ዘመን የኢየሩሳሌም ኤጲስቆጶስ በነበረው በብፁዕ አባ መቃርዮስ አማካይነት ግማደ መስቀሉ ተከፋፍሎ ቀኝ እጁ ያረፈበት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በወሎ ክፍለ ሀገር በአምባሰል አውራጃ በግሸን ማርያም እስኪቀመጥበት ድረስ በተለያዩ ቦታዎች እየተዘዋወረ አስደናቂና አስገራሚ የሆኑ ልዩ ልዩ ተአምራት ሲሠራ ቆይቷል" አሁንም ተአምራቱን እንደሚያሳይ የታመነ ነው ።

በመስቀል ብዙ ሰዎች ተጠቅመውበታል ይልቁንም የንግሥት ዕሌኒ ልጅ ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በመስቀል ኃይል ጠላቶቹን ድል አድርጓል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህንን በዓል በከፍተኛ ድምቀት የምታከብረው ያለምክንያት አይደለም ይኸውም መስቀል ከሞት ወደ ሕይወት ከኀጢአት ወደ ጽድቅ ከጨለማ ወደ ብርሃን ከባርነት ወደ ነፃነት የተሸጋገርንበት የክርስቲያኖች መጣሪያ የተገኘበት ዕለት በመሆኑ ነው ።

ስለዚህ ይህን በዓለ መስቀል ስናከብር ከታላቅ ክብርና ልዕልና ጋር ስለሆነ በዚሁ ዓቢይ የቤተ ክርስቲያናችን በዓል ላይ ተካፋይ የሆን ሁሉ የመስቀል በረከትና ረድኤት ይደርበት እያልን ምኞታችንን ስንገልጽ የመስቀልን አዳኝነትና ፈዋሽነት ያልተረዱትም በመንፈስ ቅዱስ ረድኤት የመስቀልን ድል አድራጊነት አውቀው የዛሬ ዓመት አብረን ለማክበር እንዲያበቃን እንመኝላቸዋለን ።

ሊ. ትጉሃን ገ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ልማት የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ሳይሆን በጥንተ ፍጥረት ነው እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ከመፍጠሩ አስቀድሞ የአትክልትን ቦታ አዘጋጅቶ ነበር ከዚያም ከገነት መካከል ሶስት አትክልቶች ተተክለው እንደነበሩና እነዚህም ሶስት አትክልቶች ፡ ፩ኛው ለማየት ለመብላትም ደስ የሚያሰኝ ነው ። ፪ኛውም ሕይወትን የሚሰጥ ሕይወትንም የሚያድል ሲሆን ፡ ፫ኛው ግን መልካምና ክፉውን የሚያሳውቅ ዛፍ እንደነበር በዘፍጥ ም.፪፡፰—፲ ተጽፎ ይገኛል ።

ታድያ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ከፈጠረውና ከ፬ ባሕርያት አከናውኖ ካበጀው በኋላ ቁጭ ብሎ ተቀምጦ እጁንና እግሩን አጥፎ እንዲበላ አልፈቀደለትም አትክልቶቹን እየጠበቀ እየተንከባከበ እንዲኖር ከገነት አኖረው ይላል ዘፍ ፪፡፲፭ ።

በዚህ መሠረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጆች አትክልቶችን እየተከሉ አዝርእቶችን እየዘሩ ከብቶችንና ንቦችንም የመሳሰሉትን እያረቡ ኑረዋል ።

ዛሬም ቢሆን መሬቱን እያረሱና እያለሙ ከብቶችንም እያረቡ የሚጠቀሙ በብዛት ይገኛሉ፡ የልማት ሥራ ምን ያህል ታላቅ ጸጋ መሆኑን አስቀድማ ታስተምር የነበረች ዛሬም ያልሠራ አይብላ የሚለውን ሐዋርያዊ ቃል በተግባር ስትተረጉም የምትገኘውና ለወደፊትም ሥራዋን ሣትረሳ ቤተ ክርስቲያኖችንም ጥንታዊውና በአዳምና በኖኅ ሲሠራ የነበረውን የልማት ሥራ ሳተዘነጋ በየቦታው መሬቱን በማልማት ላይ ትገኛለች ።

ምናልባት ሠርቶ መብላት ድሮ ወጥቶና ወርዶ ደክሞና ላቡን አንጠፍጥፎ ራሱን በራሱ ረድቶ መኖር በኃጢአት የመጣ የሚመስለው ሰው አይታጣም ግን ሥራ ወይም መሬቱን አልምቶ መጠቀም የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ መርገም እንዳይደለ ሲያስገነዝብ እግዚአብሔር አዳምን ይጠብቃት ዘንድ በገነት አኖረው የሚለው ቃል ዋና መመሪያችን ነው አዳም በገነት የሰራውና ጠብቃት



የልማቱ መሪ መልአከ ኃይል ኤልያስ እኒህ ናቸው

ተብሎ የታዘዘው ከመርገም በፊት እንደሆነ እንረዳለን ።

በዚህ መሠረት የዛሬው የልማት ሥራ ጸሑፋትን ለመግለጽ የምንፈልገው በሲዳሞ ሀገረ ስብከት በጌዲኦ አውራጃ ስላለው ልማት ሲሆን በተለይም ከዲላ ከተማ ፳ ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ ስለሚገኘውና በጭጩ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ስላለው ሰፊ ልማት ይሆናል ።





www.ethiopianorthodox.org

በጭጩ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አካባቢ መሬት አለ እንደሰፋቱም መጠን የተለያዩ ባሕር ዛፎችና ሌሎችም ዛፎች አትክልቶቸም ቡና የሸንኮር አገዳ የመሳሰሉት በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ተተክለው በመልካም ሁኔታ መገኘታቸውን መልአከ ሣህል ኤልያስ ከማስረዳታቸውም በላይ እኛም በዓይናችን ተመልክተናቸዋል ።

የዚሁ የጭጩ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዙርያው በድንጋይ ከመታጠሩ (ከመቀጸሩም) ሌላ በውስጡም ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ቤቶች መሠራታቸውን የአውራጃው ሊቀ ካህናት መልአከ ሣህል ኤልያስ አስረድተውናል ከጭጩ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዝቅ ብሎ የሚገኘውና የቅጽሩም ቤተ ክርስቲያን የነበረውም በመልካም ሁኔታ ታድሶ የሐዋርያው የፊልጶስ ጽላት እንዲገባበት በመጠባበቅ ላይ የሚገኝ መሆኑንም ከመግለጻቸው ሌላ እኛም ከቦታው ተገኝተን ተመልክተነዋል ።

መልአከ ሣህል ኤልያስ በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ ተተክለው ከጸደቁት ባሕር ዛፎችም በላይ በቤተ ክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ምን ያህል አዳዲስ ቤቶች የተሠሩ እንዳሉ ሲገልጹ ቤተ ልሔም የሕፃናት ማጥመቂያ የዕቃ ቤት ትልቅ አዳራሽ የእንግዳ መቀበያ የመሳሰሉት ፲፮ ያህል ቤቶች መሠራታቸውንና እነዚህም ሁሉ በአገልግሎት እዳሉ አስረድተዋል መልአከ ሣህል ኤልያስ በምን እንደተሠሩ ጠይቀናቸው ሲያብራሩ ቤቶቹ የተሠሩት በሰበካ ጉባኤ አስተዋጽኦ ናቸው ሲሉ አስረድተውናል በዚህም አውራጃ ጠቅለል አድርገው ስለልማት ሲገልጹ በዚሁ አውራጃ በሶስቱ ወረዳዎች ፴ሺህ ባሕር ዛፎች ፲፭ሺህ ቡና ፩ሺህ እንሰት የተለያዩ ዛፎች መተከላቸውንና በ፳፮ ሄክታር መሬት የስንዴ አዝመራ መዘራቱንና እሱም በመልካም ሁኔታ እንዳለ ሳይገልጹ አላለፉም ፤

የቤተ ክርስቲያንም እድሳት አውስተው ሲገልጹ በሶስቱ ወረዳዎች ፮ አብያተ ክርስቲያናት ታድሰውና በአዲስ አሠራር ተሠርተው በአገልግሎት ላይ ሲገኙ በሱማሌ ሰርጎ ገብ ከጥቅም ውጭ ሁነው የነበሩት ፪ አብያተ ክርስቲያናትም ታድሰዋል ብለዋል ።

በጠቅላላ በርካታ ኢአማንያን አምነው በክርስቶስ ስም ተጠምቀው የኦርቶዶክሳዊ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባሎች መሆናቸውን በሚገባ ጠቅለል ባለ ሁኔታ የልማቱን ይዞታ አጠቃልለዋል ። በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙት ቦታዎች ያለ አንዳች ነገር ጦም ማደር አይገባቸውም ለቦታው የሚስማማውን ተክል በመትከል የሚቀበለውንም ዘር በመዝራት በተቻለ መጠን ማልማት ተገቢ ነው ፤

ቤተ ክርስቲያን አካባቢ የሚገኙትን ቦታዎች ማልማት ሁለት ጥቅም አለው ይኸውም ፩ኛ ቦታው ሲለማ ከልማቱ በሚገኘው ምርት የቤተ ክርስቲየን አገልጋዮች ይጠቀማሉ ፤ ፪ኛው በቦታው የተለያዩ ዘሮችና አትክልቶች ሲተከሉበት መሬቱ በጎርፍ እንዳይሸረሸር በነፋስም አፈሩ እንዳይጠረግ ይረዳዋል እንደዚሁም ማንም ሰው ሊደፍረውና የቆሻሻ መጣያ ሊያደርገው አይችልም ፤

ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ያሉት ቦታዎች ጦም እንዳያድሩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና የሰበካ ጉባኤ አባሎች የሆናችሁ ሁሉ ብታስቡበት መልካም ነው እንላለን ።

ከነፈ ርግስ ማርቆስ



# ዜና ዕረፍት

## የ፳፩ ልጆች እናት የነበሩት እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው

ከአባታቸው ከአቶ ጠብቃቸው ከእናታቸው ወ/ሮ ወለተ መድኅን በ፲፰፻፹፰ ዓ/ም ኅዳር ፳፩ ቀን በሸዋ ክፍለ ሀገር በጠራ ወረዳ አምቦረጌ ተክለ ሃይማኖት ተወለዱ ፤

ከዚያም በመናገሻ አውራጃ በወልመራ ወረዳ ከነበሩት አያታቸው ጋር ተቀምጠው ሳለ ዕድሜያቸው ለአቅመ ሔዋን ሲደርስ ከካህን ወልደ ማርያም ጋር በተክሊልና በቁርባን ተጋቡ ሥርዓተ ጋብቻቸውንም የፈጸሙት በመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ አቡነ ማቴዎስ እጅ ነው ።

ይህም ዓይነት መንፈሳዊ ጋብቻ በዚያ አካባቢ ለሚኖሩ ሰዎች እንደተአምር መስሎ ታይቷቸው እንደነበር ይነገራል በዚህም የተቀደሰ ጋብቻ ከትዳር ጓደኛቸው ጋር በፍቅር እየተረዳዱ ሲኖሩ ፳፩ ልጆችን ወልደዋል ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ በልጅነት ዕድሜያቸው ስለሞቱባቸው ቢያዝኑም የቀሩትን ወቅቱ የሚፈቅደውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርትን እየቀሠሙ በምግባረ ሠናይ እንዲያድጉ አድርገዋል ።

እግዚአብሔር አምላክ ባርኮ በሰጣቸው ልጆቻቸውና በበጎ ምግባራቸው የደስታና የሰላም ዘመንን አሳልፈዋል ይህንንም ደስታና እውን የሚያደርገው ለአቅመ ሔዋን ደርሰው ጋብቻን ከመሠረቱበት ዘመን ጀምሮ በሞት ከዚህ ዓለም እስከተለዩበት ፲፱፻፹ ዓ ም ድረስ ብዛታቸው ከ፻፶፭ በላይ የሆኑ የልጅ ልጆቻቸውን በረከት ለማየት መብቃታቸውን ነው ፤

ይህ የደስታና የሰላም ኑሮ በምድራዊ ዓለም ብቻ ተወስኖ እንዳይቀር ዘለዓለማዊ ለሆነው መንፈሳዊ የዘለቄታ ሰላም እንዲሆንላቸው ባደረጉት መንፈሳዊ ጥረት ከባለቤታቸው መምህር ወልደ ማርያም ጋር ሳይነጣጠሉ በፍቅርና በመረዳዳት አንተ ትብስ አንች ትብሽ በመባባል ኑረው በ፲፱፻፶፩ ዓ/ም መዓርገ ምንኩስናን ተቀብለዋል ባለቤታቸው አባ ወልደ ማርያም ከመነኮሱ በኋላ ፪ ዓመት ኑረው ሲያርፉ እማሆይ ደብሪቱ በእግዚአብሔር ፈቃድ የጀመሩትን መንፈሳዊ ተግባር እያከናወኑ ኑሯቸውን ቀጥለዋል ።

እማሆይ ድብሪቱ በመንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ የተወሰኑ አልነበሩም በሥጋዊም በኩል ስለሀገራቸውና ስለወገናቸው የማሰብና የመቆርቆር ስሜት ነበራቸው ከዚህም የተነሣ ፩ኛ/ ጠላት ኢጣሊያ በግፍና በዕብሪት ተነሣሥቶ ሀገራችን ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ቤታቸውንና ንብረታቸውን ትተው በዱር በገደል በመዋጋት ላይ የነበሩት ልጆቻቸውን ከሌሎች መሰል ዓርበኞች ሳይነጥሉ የሞራል ድጋፍ በመስጠት ስንቅና ትጥቅ በማቀበል በቆራጥነት ስለሀገራቸውና ስለወገናቸው የነበራቸውን ፍቅር በተግባር ገልጸዋል ።

፪ኛ/ ከአብራካቸው የተገኙትን ልጆቻቸውን ብቻ ማስተማር ሳይሆን የሚኖሩበትን አካባቢ ሕዝብ ልጆችንም በትምህርት መውለድ አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበው የግል መኖሪያ ቤታቸውን ከስልሳ ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ጋር ለመንፈሳዊና ለሥጋዊ ትምህርቶች አገልግሎት እንዲውል በመለገስ የታላቅ እናትነትን ምሳሌነት አሳይተዋል ፤ ይህም ትምህርት ቤት በእርሳቸውና በባለቤታቸው ስም ተሰይሞ ከ፩ኛ እስከ ፰ኛ ዘመናዊ ትምህርት እየተሰጠበት ስለሚገኝ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን አስገኝቶላቸዋል ይህም ትምህርት ቤት የእርሳቸውንና የባለቤታቸውን ስም ለሁልጊዜ ሲያስጠራ እንደሚኖር አይጠረጠርም በዚህ ትምህርት ቤት እየተማሩ ወደከፍተኛ ትምህርት ከተላለፉትም ተማሪዎች እስከ ዶክትሬት የደረሱ ሊቃውንት ይገኛሉ ፤

መልካም ሥራ የሠራ ሰው ምስክር ስለማያጣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ጠ/ቤተ ክህነት በስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በየወሩ እየታተመ ለምእመናን የሚቀርበው ትንሣኤ መጽሔት በ፲፱፻፸፫ ዓ/ም በሰኔ ወር ቁጥር ፵፭ በወጣው እትሙ የተባረከ ጋብቻን መነሻ በማድረግ በልጅና የልጅ ልጅ አበባ እንዳሸበረቁ በዓምዱ ላይ አውጥቷቸዋል ።

እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው የዕርግና ዘመናቸውን ከልጆቻቸው ጋር ሲያሳልፉ ለበጎ ሥራ ዕረፍት ስላልነበራቸውና የተራራቁትንና በኑሮ መለያየት የተበተኑ ዘመዶቻቸውን በማስተዋወቅና በማቀራረብ ረገድ ለሰው ልጅ ፍቅር ቀናኢ እንደነበሩ በ፲፱፻፸፭ ዓ/ም የተባረኩ ልጆቻቸውን በማስተባበር ያደረጉት ታሪካዊ ስብሰባ በዕለቱ ለተገኙ ሁሉ የማይረሳ ትዝታ ነው በዚህ ምክንያት እማሆይ ደብሪቱ ርኅርኂት እናታችን ከእያንዳንዳችን ልብ ምንጊዜም የሚፋቁ አይደሉም ፤

እናታችን እማሆይ ደብሪቱ ምንም የተወደዱ ታላቅ እናት ቢሆኑም ለማንኛውም ሰው የሞት ጽዋ መቅመስ ግዴታው ስለሆነ ከመካከላችን በሞት ተለይተዋል ያረፉትም የካቲት ፳ ቀን ፲፱፻፹ ዓ/ም ነው ሥርዓተ ቀብራቸውም የተከናወነው ሥርዓተ ጋብቻና ምንኩስና በፈጸሙበትና ዕድሜያቸውን ሙሉ መንፈሳዊ አገልግሎት በፈጸሙበት በመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ነው ።



እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸው እኒህ ነበሩ

እማሆይ ደብሪቱ ጠብቃቸውና ባለቤታቸው በሕይወተ ሥጋ ሳሉ አብረው ሥርዓተ ምንኩስናን መፈጸማቸው የእርሳቸውንና የባለቤታቸውን ጽኑ የሆነ መንፈሳዊ ዓላማ የሚያረጋግጥ ነው ባለ



www.ethiopianorthodox.org

# መናፍስትን መዋጋት

ሐሰተኛ የሐሰት አባት ነውና በየጊዜው በሚረጨው የተንኮል መርዝ ዓለምን ሲያበጣብጥና ሲያተራምስ ይኖራል የሰይጣን ርኩስ መንፈስ የፈጠራቸው ቂም ፡ በቀል ፡ ጥላቻ ፡ ዝሙት ፡ ምቀኝነት ፡ የሐሰት ፡ ትምህርትና ትዕቢት ፀላኤ ሰናያት ዲያብሎስ በሰው መካከል የሚበትነው የመልካም ተግባር እሾህና አሜከላ እንደሆነ መንፈሳውያን አባቶችና ቅዱሳት መጻሕፍት ይልቁንም ከሁሉም በላይ የሃይማኖታችን መርህ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ።

አባይ ጠንቋይ አስማተኛና ኮከብ ቆጣሪ ሐሰት እየተናገሩ የዋሐንን እያታለሉ ሕዝቡ ለፍቶ ደክሞ ያገኘውን የሥራ ውጤት ያለ ይሉኝታ ሲበዘብዙና ሲመዘብሩ ኑረዋል ። ዛሬም ቢሆን አልፎ አልፎ ቅሪቱ አልጠፋም ነገር ግን የሰው ንቃተ ሕሊና እያደገ መንፈሳውያን መጻሕፍትን እየመረመረ ዘመኑ በፈጠረው የሳይንስ ጥበብም እየተጠቀመ ሲሄድ የመናፍስት እኩይ ተግባር መልኩን ለውጦ የማታለያ መንገዱን በአዲስ መስመር ቀይሶ ወጣቱን ትውልድ ለማደናገር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ።

አንዳንድ የሐሰት ጸሐፎች እየተባዙ ሰው እንዲያነባቸውና በተአምራቸው አፍላቂነታቸው እንዲያመልካቸው እየሆኑ ነው የአጉል ባህል ውጊያ በሚያስፈልገው በአሁኑ ወቅት ቤተ ክርስቲያን ከማስተማርና መከራ ከመመለስ ችላ ማለት የማይገባት ስለሆነ ከየአቅጣጫው የሚመጡትን ያጉል እምነት አራማጆችንና ፍሬ አልባ የሐሰት ነቢያት የሚፈጥሩትን የአእምሮ ጭንቀት ሁከት በስብከትና በአሉባልታ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የሐሰት መናፍስትን በፅኑ ትዋጋለች ።

ሆኖም የወጣቱን ልብ እየሠለቡ ከክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲርቅ የሐሰት መርዝን በመርጨት ላይ ባለው የዘመናችን መናፍስት በሆነው በራምታ እምነት ላይ የውጊያ እጇን ታነሣለች ። ስለራምታ አጫጭር መግለጫዎች መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

የራምታ እምነት ሙታንን ከሕያዋን ጋር አገናኝቼ የማነጋገር ኃይል አለኝ ፡ አሜሪካ ካለው ዘመዳችሁ ቃል በቃል እንድትነጋገሩና በአይነ ሥጋ እንድትተያዩ ማድረግ እችላለሁ ይኸውም እዚሁ አዲስ አበባ ሆናችሁ የሚል ፡ ኤስትራ ትራቦልንግ ወይም መንፈሣዊ ጉዞ አድርጋችሁ የዓለምን ውብ ሠፈሮች ቶክዮ ፡ ኒውዮርክ ፡ ዋሽንግተን ፡ ለንደን ፡ ሮማ ፡ ስቶክሆልም ፡ ወዘተ ... የመሣሠሉትን ላስጎብኛችሁ የምችል ረቂቅ መንፈስ ነኝ ብሎ የዓለምን አራት አቅጣጫዎች በልዩ ኃይል የጨበጠ መሆኑን እራሱን የሚሠብክ መንፈስ ነው ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይኸው ሐሰተኛ የጋፉት ነቢይ በሚወለድበት ጊዜ የትውልድ አገሩ የቲቤት ጠንቋዮች ልዩ ኃይል ያለው አዋቂ ዛሬ ተወለደ እያሉ እንደዘመሩለት ስለራምታ የሕይወት ታሪክ ከተፃፈው ለማግኘት ችለናል ከዚህ የምንረዳው ቁም ነገር እድል ነጋሪዎችና ኮከብ ቆጣሪዎች የሚመሠክሩለት ሰው እራሱ ዓለምን በረቂቅ ማታለያ ስልት ለማወናበድ የመጣ ነው ከማለት በስተቀር ሌላ ቃል ወይም አስተያየት ሊኖር አይችልም ።

፳ኛው ክፍለ ዘመን በሳይንስና በቴክኖሎጂ መጥቀው የምድራችንን ስልጣኔ ከዕለት ወደ ዕለት የደቂቃ እድገት እየጨመረ ልቆ ለሰው ምርምር ነፃ ሕይወት እየተስፋፋ በእንፃሩ ደግሞ ሕሊናን የሚያዋዥቅና አስተሳሰብን ወደ ኋላ የሚጎትት አጉል ባህል የእምነት እንቅፋት ተቀባይነት የሚኖረው አይመስልም ከዚህም ጋር አምላካችን እግዚአብሔን መሆኑን አምነን የተቀበልን ክርስቲያኖች ለእምነታችን መመሪያ ከመጽሐፍ ቅዱስ የበለጠ የሕይወት መመሪያ ሊኖረን ስለማያስፈልግ በሐሰት ፍልስፍና መወናበድና ሰው ሰራሽ አምልኮን መከተል ተቀባይነት አይኖረውም በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ቃልን ኃይል አድርገን ከዘመናችን ሳይንሳዊ እውቀቶች በማዛመድ ጎታች መናፍስትንና የሐሰት ፍልስፍናን መዋጋት ተጨባጭነት በሌለው ተአምራት ማመን በማናውቀው ነገር አጉል ተስፋ መመራት ልባችን ውስጥ ኑፋቄን መጨመር የለብንም ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተለውን የሚያወራውን እና የማያጠራጥር ትምህርት ይሰጣልና ። የዲያብሎስን የተንኮል ሥራ መቃወም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን የጦር መሣሪያ በሙሉ ልበሱ ምክንያቱም የእኛ ውጊያ ከሰዎች ጋራ ሳይሆን በዚህ በጨለማ ዘመን ከሚሠሩት ገዥዎች ከባለ ስልጣኖች ከዓለም ኃይሎችና በሰማይ ካሉት የርኩሳን መናፍስት ጋር ነው ።

የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ኤፌሶን ም·፮·ከ ቁ·፲፩—፲፪ ያለውን ቃል ገዦች የምድር ኃይሎች የተባሉት በቤተ ክርስቲያናችን ትርጓሜና በመጽሐፍ ቅዱስ አባባል አጋንንትና ሌሎችም ርኩስ ተግባር የሚፈጽሙ የዲያብሎስ ተከታዮች ማለት ነው ።

ስለዚህም ቤተ ክርስቲያናችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የዋጃት ርትእት ሃይማኖት በመሆኗ ርኩሳን መናፍስትን መዋጋት ተዋግቶም በእግዚአብሔር ኃይል ማሸነፍ ባላት ሃይማኖታዊ ብቃትና መንፈሳዊ ዓላማ በመነሣት የራምታን መንፈስ እና የሐሰት ፍልስፍና ከንቱ መሆኑን በይፋ ታጋልጣለች ።

የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በግል የሚያውቃት አንዲት ክርስቲያናዊት ወጣት የሰጠችውን አባሪ የእንግሊዝኛ ደብዳቤ ከዚህ እንደሚከተለው ወደ አማርኛ መልሶ ያቀርበል ። የተጻፈው እምነሲዝም ዳውንደሽን (የመንፈሳዊ ድርጅት) ከሚባል አድራሻውን ያልገለፀ ክፍል ከላይ ለተጠቀሰችው ወጣት የደረሳት ነው...ሃይማኖት ይህ ደብዳቤ ስለደረሰሽ እንኳን ደስ ያለሽ ብዙ ሰዎች ይህ ደብዳቤ ደርሷቸው በአግባቡ ስለተጠቀሙበት የመልካም እድል ታዳሚዎች ሆነዋል ሜሪ ሐንሰን የተባለች የቦስተን ከተማ ኗሪ አራት ሚሊዮን የሎተሪ እድል ደርሷታል ዋሽንግተን ለሚኖሩ ሮበንሠን ለሚባሉ የሰባ አመት አዛውንት ደግሞ ሌላ እድል አስገኝቶላቸዋል ይኸውም ለእድሚልክ የሚሆን የመድህን ዋስትና ወረቀት ነው ብራዚል ውስጥ የምትኖረው የአስራ አምስት ዓመት ወጣት ሴት ሽባ ነበረች ይህ ወረቀት ሲደርሳት ተፈወሰች ይላል ።

ቀልድ አይደለም ይልና ፍሬ ሐሳቡን ሲያስፋፋ ሽብር መፍጠሩን ይቀጥላል ሜክሲኮ ውስጥ ለአንድ የአስራ ስምንት ዓመት ወጣት ይህ ደብዳቤ ደርሶት የታዘዘውን ባለመፈፀሙ በአንድ ቀን አዳር መላ ሰውነቱን ታሞ መላወስና መንቀሳቀስ አቅቶት ሽባ ሆኗል በማለት የሞቱትንና ልዩ ልዩ አደጋ የደረሠባቸውን አምስት ሰዎች ጠቅሶ አንቺም እንደታዘዝሽው ይህን ደብዳቤ በመኪና ጽሑፍ አባዝተሽ መልካም እድል ለምትመኝላቸው ለሀያ ሰዎች ካደልሽ በወር ውስጥ ሥራ ታገኚያለሽ ካላደልሽ ግን ይህ ደብዳቤ በደረሠሽ በ፺፮ በዘጠና ስድስት ሰዓቶች ውስጥ ትሞቻለሽ ሲል ያስጠነቅቃታል ።

ነገር ግን ሃይማኖት በእግዚአብሔር አዳኝነት የምታምን ሐቀኛ ክርስቲያን በመሆኗ የታዘዘችውን በእሷ ላይ የደረሠ መልካም እድልም ሆነ ቀሣፊ ኃጢአት እንደሌለ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ይገልፃል ።

እንደሚታወቀው አእምሮአችንን በጭንቀት ሕሊናችንን በሁከት እንዲጨልም ለራሣችን መሞት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል ስለሆነም የዘመን መለወጫ በአልን በባእድ አምልኮ አጅበን በአጉል ምክንያቶች ለውቃቢ ደስታ ለዛር እርካታ ብለን የበግና የዶሮ ምርጫ እያደረግን እራሣችንን የምናታልል ከሆንም ከላይ እንደተመለከትነው የራምታ መንፈስ የጭንቀትና የሁከት በሽታ በራሳችን ላይ የምንፈጥር መሆናችንን መገንዘብ ይገባል ይህንንም ስናደርግ ሌላ የምናገኘው አዲስ እድል ወይም የተሣሣተ አመለካከትን የሚቸረን ልዩ ልዩ ጥቅም ፈፅሞ አይኖርም ።

ቀለመ ወርቅ መአሾ

## የግብርና በረከት

(ከገጽ ፲፰ የዞረ)

ግዛው ይባላሉ ወደ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት መለስ ስንል ደግሞ በዚህ ዓይነቱ የሥራ እንቅስቃሴ ቦታ ያላቸው አሉ ታድያ በዚህ ሥራ የቱን ያህል ምሳሌ ሆነዋል?

የቦታም ጥበት ያለባቸው አሉ እኒህም ከግብርና ሥራ አንደኛውን የዛፍ ክፍል በማልማት እንደሚገኙ እሙን ነው ከሆነም ሁሉም እንደየአመችነቱ ቢዘጋጅና ቢያለማ የግብርና በረከት ሊሟላና ተገቢውን ክፍል በመጠኑም ቢሆን ከማንጋጠጥ ሊያድነው ይችላል ።

ስለዚህ ልዩ ልዩየምግብ አትክልቶችን እንደየአመችነቱ ቢያለሙ የቤተ ክርስቲያኒቱን ገቢ ለማጠናከር ከመቻላቸውም በላይ የአካባቢውን ተጠቃሚ በቀላሉ ሊረዱ ይችላሉ ።

በለጠ አበበ

---

ቢታቸውም ከሞቱ በኋላ ዓቅማቸው እስከ ደከመ ድረስ ቀዶም ሲል ሲያደርጉት የነበረውን መልካም ሥነ ምግባርና በጎ አድራጎት ሁሉ ሳያጓድሉ እንግዶችን በመቀበል ዝክር በመዘከርና የተቸገሩትን ሁሉ በመርዳት በአጠቃላይ ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን ተወጥተው ያለፉ እናት ናቸው ።

የእናታችን እማሆይ ደብሪቱ ዜና ሕይወታቸውና አኗኗራቸው ለሌሎች እናቶች ትምህርትና መመሪያ ይሆናል ብለን እናምናለን ።

ከቤተሰቦቻቸው





www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

በዚህ የግብርና በረከት ዓምድ ግብርናን የሚመለከት መልእክት ሲተላለፍ ቆይቶ ነበር ፡ ነገር ግን ሲተላለፍ የቆየው መልእክት ተቋርጦ በመቆየቱ ከአንባብያን ለምን እንደቆመ የተደጋገመ ጥያቄ ሊቀርብ ችሏል ።

በቀረበልን ጥያቄ መሠረት የአምዱ መኖር ጠቃሚ መሆኑን በመገንዘብ ግብርናን የሚመለከት ትምህርት ከባለሙያዎች በመቅሰምና ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር በማገናዘብ ለአንባብያን የምናቀርብ መሆናችንን እንገልጻለን ።

እንደሚታመነው ከዚህ የግብርና በረከት የማይሳተፍ ፍጡር የለም ምክንያቱም ለሁሉ ምግብ ያስፈልገዋልና ፡ እኛም ከበረከቱ ለመጠቀምና በረከቱን ለተጠቃሚው ሁሉ ለማዳረስ ይቻል ዘንድ በግብርና ሙያ የቅርብ ግንኙነት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመነጋገርና ከግብርና ሚኒስቴር የሚዘጋጁ መጽሔቶችን በመያዝ አስፈላጊውን ዘዴ እናቀርባለን ።

የግብርናን በረከት ለማትረፍረፍ ሁሉም በየበኩሉ የሥራው ተሳታፊ ቢሆን ሙሉ በሙሉ ባይሆንም ብዙ ነገሮችን ከጓሮው ወደ (ጉተራው) መገልገያው ሊሞላ ይችላል ።

ግብርና ሲባል ግን የእህል ዓይነቶችን ብቻ ማምረት አይደለም፡ ከዳቦ ጋር ሊዛመዱ የሚችሉ የምግብ አትክልት ዓይነቶችን ጭምር እንጂ እህልና የምግብ አትክልቶችን ብቻ በማዝመርም በረከቱ የተሟላ አይሆንም ፡ ስለዚህም ዓይነቶችን አብሮ ማልማት ጠቃሚ ይሆናል ።

በግብርና ሙያ የተሰማራና ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ምግብ ሲያገኝ መጠለያ ያስፈልገዋል ፡ በመጠለያውም የቤት እቃዎች ያስፈልጉታል ፡ ማገዶና ሌላም ዓይነት ዝግጅት ስለሚያስፈልገው የዛፍ ልማት የግድ አስፈላጊው በመሆኑ እነዚህ ነገሮች አብረውት ሊኖሩ እንደሚገባው አምኖ ትኩረት ሊጥልበት ይገባል።

በግልጽ እንደሚታየው የግብርናን በረከት ለማግኘት የሚጥረው የሕዝብ ቁጥር በቀላሉ የሚገመት አይደለም ። ከሆነም ዘንድ ሁሉም ከጓሮው በመጀመር የግብርናን ፍሬ ቀምሶ ቢያቀምስ የግብርና በረከት የሞላ ይሆናል ብለን እንገምታለን ። በሌላ በኩል የምንመለከተው በዓለም የሚኖር ፍጡር ሁሉ በዳቦ ብቻ መኖር እንደማይችል ታምኖ የሥራ ክፍፍል ተሰጥቶታል ይኸውም አራሹ እንዲያርስ ፡ ምሁሩ እንዲያስተምር ፡ አስተዳዳሪው እንዲያስተዳድር የየፋብሪካው ሠራተኛ እንዲያመርት ነጋዴው እንዲነግድ ሠራዊቱ ድንበር እንዲጠብቅ ወዘተ ሆኖ ቆይቶአል ።

ይህ አሠራር ቢደነገግም በመጀመሪያ ደረጃ ሊጠናከር ግድ ሆኖ የተገኘው የግብርናው ክፍል ነው ምክንያቱም ገበሬው ምሁሩ ፡ ሠራዊቱና በየመስኩ የተሠማራው ዳቦ ያስፈልገዋልና ነው ።

ስለዚህም የግብርና በረከት በተትረፈረፈ መንገድ ተጠናክሮ ለበላተኛው እንዲዳረስ ጥረት ተደርጎበታል እየተደረገበትም ነው ሆኖም የጥረቱን ፍሬ ለማግኘት የእግዚአብሔር በረከት እንዳይለየው ጸሎት አስፈላጊ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ የግብርናን በረከት ለማግኘት ሁሉም በየጓሮው የሚያደርገው ሙከራ ደስ የሚያሰኝና በረከቱን ለማትረፍረፍ የሚያስችል ነው ።

በየጊዜው በምሳሌነት የምንጠቅሳቸው የ፹ ዘመን የዕድሜ ባለፀጋ የሆኑትን አቶ ስሜ አመነን ነው ።

አቶ ስሜ አመነ በዚህ ዕድሜ ሆነው ደከመኝ ሳይሉ የሚያሳዩት የጓሮ አትክልት ውጤት ተመልካቹን ሁሉ ለዚህ ዓይነቱ ሥራ የሚቀሰቅስ ነው ፡ ይኸውም ወደ ሌላ ትጉህ ሠራተኛ በማንጋጠጥ ራስን በራስ ለመርዳት የሚያስችል በመሆኑ በአርአያነታቸው የሚመሰገኑ ናቸው ። ወደ ሌላው አካባቢ መለስ ስንል በጓሮ አትክልት አያያዝ ለአካባቢው ባለጓሮ ምሳሌ የሆኑ አንድ ምሁር አሉ ፡ እኒህም ምሁር የተሰለፉበትን የአመራር ሥራ ሲያከናውኑ ውለው ደከመኝ ሳይሉ ወደ ጓሮአቸው ገባ በማለት ሲቆፍሩ ሲተክሉ ፡ ውሃ ሲያጠጡና በአጠቃላይ ተገቢውን ሥራ ሲያከናውኑ ሲታዩ የሚያተጉ ናቸው ።

ምሁሩ በጓሮአቸው ጐመን በቆሎ የተለያዩ የቃሪያ ዓይነቶች ቲማቲም ፡ ቆስጣ ፡ ሰላጣ ፡ ቀይሥር በመትከል ከራስ ችግር አልፈዋል ። ይህንን ሙከራ በማስፋፋት ሽንኩራ ፡ ሙዝ ፡ ቡና ኮባ ወዘተ በማልማት የሥራቸው በረከት ሲታይ በዋናው የግብርና መስክ እንደሚለማ እንጂ የጓሮ አትክልት ነው ለማለት አያስደፍርም የምሁሩ እንቅስቃሴ ጐረቤቱን ሁሉ ቀስቅሶታል ። የጓሮ ጥበት ካልሆነ በቀር አካባቢው ራሱን በራሱ እንዲረዳ አስችሎታል እኒህም ምሁር አቶ አልታየ

(ወደ ገጽ ፲፯ ዞሯል)



# ሥርዓተ ቅዳሴና ጥቅሙ

ሥርዓተ ቅዳሴ ማለት በቅዳሴ ጊዜ ምእመናን ለማስቀደስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ ቀሳውስትና ዲያቆናት የቅዳሴውን ጥቅም ለምእመናን በአማርኛ እየተረጐሙ ማስተማር አለባቸው ምእመናንም ከተማሩት ጥቅሙን ተረድተው ቅዳሴ ሲያስቀድሱ ዓይናቸውንና ልቦናቸውን ሳያባክኑ በሰቂለ ሕሊና ሁኖ ቆሞ ማስቀደስ እንደሚገባቸው ካህናትም ለምእመናን አብነት ለመሆን በሥነ ሥርዓት ቁመው ማስቀደስ እንደሚገባቸው የሚመራና የቅዳሴ ጥቅሙ እንዴት እንደሆነ የሚያሳይ ቃል ተጽፎ ይገኛልና ይህንን መፈጸም ነው ።

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ ብሎ አምኖ ክርስቲያን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ከክፉ ነገር ተጠብቆ ኃጢአቱን እያሰበ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን እየለመነ መቆም ይገባዋል እኛ ባላወቅነው እርሱ ባወቀው ኃጢአታችን ይቀሥፈን ይሆን እያለ ባለፈው ይቅር በለን ለሚመጣው ጠብቀን ፡ ፍቅርህን አሳድርብን እያለ ማልቀስ ይገባል ፡

የክርስቶስ ፍቅር ካደረ ኃዘን ልቅሶ የግድ ይመጣል ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሌላ ሥጋዊ ነገር ማሰብ አይገባም ፡

ማረኝ ማረኝ በሚሉበት ጸጋውን ክብሩን በሚያገኙበት ጊዜ ሌላ ትርፍ ነገር ማሰብ አይገባም ፡ ቄሱ ስለምእመናኑ የሚጸልየውን ማድመጥ ተገቢ ነው አዕምዕ ቃሎ ለካህን ወስማዕ ዘይስእል ሥርዬተ በእንቲአከ ወበእንተ ኩሎሙ ኃጥአን ያናሕሲ ሎሙ አምላኮሙ እንዲል ሥርዓተ ቅዳሴ ተመልከት ምእመናኑም ለቄሱ ሊጸልዩለት ይገባል ከቀሣፊ መልአክ ሠውረው መሥዋዕቱን ወደህ ተቀበለው እያሉ በቅዳሴ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ መውጣት አይገባም ጽኑዕ ሕመም ካላገኘው በስተቀር እትው እስከ ሚባል ድረስ ቆሞ ማስቀደስ ይገባል ።

ሐዋርያትም በሲኖዶስ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቁሞ የማያስቀድስና ሥጋውንና ደሙን የማይቀበል ምእመን ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ ብለዋል የሐዋርያትንና የሰለስቱ ምዕትን ቃል አልቀበልም አልሰማም ብሎ ከሚፈረድበት ቁሞ ማስቀደስ ይሻላል ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቅዳሴ ጊዜ ቁሞ የማያስቀድስ ከእኔ ጋር አንድ የማይሆን ጠላቴ ነው ምእመናንን ይበትንብኛል እንዳላድርባቸውም ያደርገኛል ብሏል ማቴ ም.፲፪ ቁ.፴ በቅዳሴ ጊዜ ቄሱ አለቃው መሪጌታው ደብተራው ወጥተው ይሔዳሉ እነርሱ ወጥተው ሲሔዱ አይተው ምእመናን እነዚህ የተማሩት ወጥተው መሔዳቸው ቁሞ ማስቀደስ የማይጠቅም ቢሆን ነው ብለው እነሱን ተከትለው ወጥተው ይሄዳሉ ።

ይሁዳ በምሴተ ሐሙስ ከክርስቶስ ተጣልቶ ከሐዋርያት ተለይቶ ከአይሁድ ጋር ሴራ መትቶ ወጥቶ እንደሄደ ዛሬም በቅዳሴ ጊዜ ሳያስቀድስ ወጥቶ የሚሔድ እንደ ይሁዳ ነው ዲያብሎስ ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አልሆንም እግዚአብሔርን አላመሰግንም ለእርሱም አልሰግድም ብሎ ከማኅበረ መላእክት እንደተለየ በቅዳሴ ጊዜም የሚወጣ ሰው ከእግዚአብሔር መለየቱ ነው ምድራዊ የሕዝብ መሪ በመጣ ጊዜ አማኒ እልል ብሎ አክብሮ ተቀብሎ ያገባዋል ታጥቆ በሥርዓት ደጅ ይጠናዋል ፡

ሽፍታ አመፀኛ ግን የሕዝብ መሪ በመጣ ጊዜ ሸሽቶ ወደ በረሃ ይገባል ከዱር ይሸሸጋል እንደዚሁም ሁሉ የሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ ሥጋ ከቤተ ልሔም ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ታጥቆ ቆሞ ደጅ እንደመጥናት ሁሉ ወጥቶ መሔድ ከክርስቶስ ፊት ሸፍቶ ለሌላ ጌታ ለዲያብሎስ አገልጋይ መሆን ነው ሌሊቱን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ቁሞ ሲጸልይና ሲዘምር አድሮ በቅዳሴ ጊዜ ወጥቶ የሚሔድ ሰው ዋጋ የለውም ለዚህም ነገር ምሳሌ አለው ፡

ከሕዝብ መሪ ዘንድ ጉዳይ ያለው ሰው ደጅ ይጠናል የሀገር መሪውም ጉዳዩን እስኪፈጽምለት ድረስ ባልደረባ ሰጥቶ ቆይ ተጠባበቅ ይለዋል ያም ሰው ደጅ የጠናበት ጉዳዩ ሳይፈጽምለት ወደ ፈለገው ወጥቶ ይሔዳል የሕዝብ መሪውም ጉዳዩን አይቶ ሊፈጽምለት ቢያስፈልገውና ቢያስጠራው የሚታጣ ሰውን ይመስላል ዛሬም ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ሲጸልይ ሲደክም አድሮ ዋጋውን ክብሩን በሚያገኝበት በቅዳሴ ጊዜ ወጥቶ የሚሔድ ሰው ይህን ይመስላል ፡

በቅዳሴ ጊዜ ወጥታችሁ ሒዱ የሚል መጽሐፍ አይገኝም ቁሞ ማስቀደስ የማይችል በሽተኛ ወጥቶ ከሚሔድ ተቀምጦ ማስቀደስ ይሻላል ችሎታ ያለው ቁሞ ተሰጥዎን መቀበል ነው ፡

ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ዋዛ ፈዛዛ ሣቅ ሥላቅ ትርፍ ነገር መናገር አይገባም በቅዳሴ ጊዜ ወዲያ ወዲህ ማለትም ክልክል ነው ወኢትኩን በጊዜ ቅዳሴ ወጸሎት ዘተሐውር ከሃ ወዝየከመ አጋንንት እንዲል ፡

ከቤተ ክርስቲያን ገብቶ ከአንድ ቦታ ቁሞ ልብን ሳያባክኑ ወዲያ ወዲህ ማየትን ትቶ ማረኝ



www.ethiopianorthodox.org

ማረኝ እያሉ ማዘን ማልቀስ ይገባል ቤተ ክርስቲያንን የሚጠብቁ በቀን ፺፱ በሌሊት ፺፱ መላእክት አሉ ይባላል እነዚህም በቅዳሴ ጊዜ በቤተ መቅደስ ዙሪያ ቁመው ቅዳሴው እስኪፈጸም ድረስ ይጠብቃሉ ጌታችን በመልዕልተ መስቀል በዕለተ ዓርብ ተሰቅሎ ሳለ በመስቀሉ ዙሪያ መላእክት እንደ ቅጠል ረግፈው እንደ ሻሽ ተነጥፈው ሰግደው ወድቀው እንደዋሉ ዛሬም በቅዳሴ ጊዜ እንደዚያ ሁነው እስከ ቅዳሴው ጸሎት ፍጻሜ ድረስ ይቆያሉ ይሰግዳሉ ፡

በቅዳሴ ጊዜ ወንጌል ሲነበብ ኪዳን ሲደርስ ከቤተ ክርስቲያን ወጥቶ የሚሔድ ሰውን መልአክ ውቃቢው ይለየዋል ሰይጣን ግን ከደጅ ቆይቶ ልጄ ወዳጄ መጣህልኝ ብሎ ይቀበለዋል በዚህ ጊዜ ታላቅ ደዌ ያድርበታል ይህ መቅሠፍት የሚመጣው ሕጉንና ትእዛዙን በማፍረስ ነው ፡

ዲያቆኑ ስገዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ሲል ሕዝቡ ሁሉ ይሰግዱ ፍትሐት ዘወልድንና በእንተ ቅድሳትን በግንባራቸው ወድቀው ይሰሙ መስገዳቸው መውደቃቸው ኃጢአተኞች በደለኞች ነን ማረን ይቅር በለን ሲሉ ነው ፡

ዛሬም በደለኛ ከመሬት ወድቆ ነው ማረኝ የሚል አሁንም ዲያቆኑ በቅዳሴ ጊዜ ስገዱ ለእግዚአብሔር ሲል አልሰግድም ማለት ኃጢአት የለብኝም ማለት ነው ዲያብሎስ ለፈጣሪህ ስገድ ቢሉት ስገዱልኝ እንጂ አልሰግድም አመስግን ቢሉት አመስግኑኝ እንጅ አላመሰግንም አለ በዚያን ጊዜ ባደረ የጨለማ ቁርበት ጠቅሎ አንጦርጦስ አወረደው ፡

አሁንም በቅዳሴ ጊዜ ለእግዚአብሔር አልሰገድም ተሰጥዎም አልቀበልም የሚል እንደ ዲያብሎስ ውርደት ያገኘዋል የሚሰግድባቸውም ጊዜያት ፩ኛ. ጸሎተ ንስሐ ሲደገም ፪ኛ. ፍትሐት ዘወልድና በእንተ ቅድሳት ሲነበብ በቅዳሴም መካከል የሚጸለየው ዲያቆኑ ተንሥኡ ሲል እግዚአ ተሣሃለነ አቤቱ ይቅር በለን ማለት ነው ቄሱ ሰላም ለኩልክሙ ሲል ምስለ መንፈስከ እንደቃልህ ይደረግልን ማለት ነው ዲያቆኑ ጸልዩ ሲል አቡነ ዘበሰማያት ኀድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ ምንሱት እያሉ መጸለይ ነው ፡

ከዚህም የበለጠ ጸሎት የለም ይህን ትቶ ሌላ ትርፍ ጸሎት መጸለይ በቅዳሴ ጊዜ አይገባም የምድራዊ ሹም ደብዳቤ ሲነበብ ደፍሮ የሚስቅና የሚናገር አይኖርም በዚህም አንፃር የሰማያዊ የክርስቶስ ቃልም ሲነበብ መናገር ከፍ ያለ ፍዳን ያመጣል ካህኑ ዳዊት ከጳውሎስ ከግብረ ሐዋርያት ከወንጌል ጠቅሶ አምጥቶ ቀምሞ መምከር ማስተማር ነው እንጅ በቃል ንጹሕ ነኝ ብሎ እጅን መታጠብ ብቻ ከኃጢአት ሊያነፃ አይችልም ለምሳሌ ያደፈን ልብስ በእንዶድና በሳሙና ደህና አድርጎ ካላጠቡት እንዲያው ንጹህ ሁን ቢሉት አይነፃም ፡

አሁንም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ የክርስቶስን ደም ይቀበል ፡ የማይቀበል ክርስቲያን ክርስቲያን አይባልም እንዳልተጠመቀ ነው ለዚህም ማስረጃ ሐዋርያት ወኢተመጠወ እምቁርባን ይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ሥጋ ወደሙን ያልተቀበለ ምእመን ከቤተ ክርስቲያን ይሰደድ ሕገ እግዚአብሔርን አፍርሷልና ብለዋል ለምን የተባለ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን ማለት ከክርስቶስ የተወለዱ ምእመናን የሚሰበሰቡባት ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉባት ትምህርተ ሃይማኖት የሚማሩባት ማለት ነው በደልኩ ተመለስኩ ያለ እንደሆነ ንስሐውን እስኪጨርስ ይለይ ብለዋል ፡

ሥጋ ወደሙ የማይቀበል ምእመን ጽንዓተ ነፍስ የለውም ክርስቶስም አያድርበትም ትንሣኤ ነፍስም የለውም ፡

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመንጌል ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ ከእኔ ጋር ተዋህዶ ይኖራል እኔም ከእርሱ ጋር ተዋህጄ እኖራለሁ ብሏል ሰው ያለማኅደር አይኖርም የሰይጣን ማህደር ሁኖ ከመኖር የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሁኖ መኖር ይሻላል በስም ክርስቲያን ነኝ ማለት አይጠቅምም የክርስቲያን ሥራ ሠርቶ በክርስቲያን ሕግ ጸንቶ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት ሴት በአንድ ወንድ በሚለው ሕግ ተወስኖ አሥራቱን በኩራቱን አውጥቶ አጽዋማትን በዓላትን እያከበሩ ሥጋወ ወደሙን እየተቀበሉ መኖር ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ይገባዋል ፡

ነገር ግን ከሕገ እግዚአብሔር ወጥቶ እንደፈቀደ ይኖር የነበረ ሰው ሲታመም አቁርቡኝ ያለ እንደሆነ ተናዞ ንስሐውን ተቀብሎ ከገንዘቡ ሲሶውን ለነዳያን መጽውቶ እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ሴትም ሆነች ወንድ በአንድ ጋብቻ ተወስኜ ሥጋ ወደሙን እየተቀበልኩ በሕገ እግዚአብሔር ጸንቼ እኖራለሁ ወደ ቀደመ ግብሬ አልመለስም ብሎ ቃል ኪዳን ገብቶ ይቀበል ከዚህ ሁሉ ነገር በ፵ ቀናችንና በ፹ ቀናችን ሥጋ ወደሙን ተቀብለን የለም እርሱ አይበቃንም የሚሉ አይጠፉም ይሆናል በዚህ ብቻ ክርስቲያን አይባሉም ፡

ለዚህም ምሳሌ አለው መብራት አንድ ጊዜ ያበሩታል በየጊዜው ፈትሉን ዘይቱን ካልሰጡት ይጠፋል እንጅ ሲያበራ አይኖርም እንደዚሁም ሁሉ ሰውም አምኖ ተጠምቆ ሥጋ ወደሙን እየተቀበለ በክርስቲያን ሥርዓት ካልኖረ በ፵ ቀንና በ፹ ቀን የተቀበለው ልጅነት ይጠፋል ልጅነቱም ከጠፋ በግብረ አሕዛብ መኖሩ ነው ከዚህ ሌላ ምሳሌ አለ ሰው ከናቱ ከአባቱ አንድ ጊዜ ይወለዳል ወተት ፍትፍት እየመገቡ በየጥቂቱ ያሳድጉታል ያንንም ልጅ ሁል ጊዜ አይወልዱትም ፡ እንደዚህም ሁሉ ሰውም አንድ ጊዜ ከሥላሴ ይወለዳል አባት እናት ልጅን በወተት በፍትፍት እንደሚያሳድጉት ሰውም ሥጋውንና ደሙን እየተቀበለ ያድጋል በየጥቂቱ እያለ ከፍጹም ዕውቀት ይደርሳል ስለዚህ ጥምቀትን አንድ ጊዜ ሥጋ ወደሙን ሁል ጊዜ እንድንቀበል ታዟል ።

ሰው ሥጋዊ ምግብ ያጣ እንደሆነ ይሞታል ነፍስም መንፈሳዊ ምግብ ሥጋውንና ደሙን ያጣች እንደሆነ ትሞታለች ሞታ ለነፍስ ርኅት እምእግዚአብሔር እንዲል ሥጋ ወደሙን የሚቀበል ሰው የሥላሴ አንድነት ሦስትነት ምልዓት ስፋት ርቀት ፡

ከሶስቱ አካላት ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው መሆኑን በዮርዳኖስ መጠመቁን ስለኛ ብሎ በአይሁድ እጅ ብዙ ፀዋትወ መከራ ተቀብሎ ተሰቅሎ መሞቱን በጦር ጐኑን ተወግቶ ደምና ውሃ ማፍሰሱን ተቀብሮ ሙቶ መነሣቱን ማረጉን ለሐዋርያት ቋንቋ መግለጹን ዳግመኛ መምጣቱን ኀብስቱ ተለውጦ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ደመ መለኮት መሆኑን አውቆ ተምሮ መቀበል ይገባል ፡

ከተቀበሉም በኋላ እጅ እግር መታጠብ ራቁት መውጣት ስጊድ አስተብርኮ ምራቅ እንትፍ ማለት ከሰውነት ደም ማውጣት ጥፍርን መቁረጥ ራስን መላጨት ሩቅ መንገድ መሔድ ሐሜት ሙግት ከውሽባ ቤት መግባት ያለልክ መብላት መጠጣት ከሴት ጋር በግብረ ሥጋ ግንኙነት ማድረግ በዚያን ዕለት በፍጹም ክልክል ነው ፡

እንግዲህ በሥርዓተ ቅዳሴ ውስጥ የተጻፈውንና የተደነገገውን ዋና ዋናውን ገልጸንላችኋልና በተግባር እንጠቀምበት መሮጥ መውጣት መውረድ ማወቅ መሥራት ጉልበትና ዓይን ሳይደክም ነው በመንፈሳዊ በኩልም በሕግ መወሰን ሥጋ ወደሙን መቀበል ሃይማኖትንና ምግባርን ተምሮ መጠበቅ ከልጅነት ጀምሮ ነውና ሞት ሳይቀድመን በዚህ በሥርዓተ ቅዳሴ የተጠቀሰውን ተመልክተን ለመንፈሳዊ ነገር እንሽቀዳደም ።

አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም

---

## ደብዳቤዎች

(ከገጽ ፭ የዞረ)

በኋላ ግን የተለያዩ ስሞችን እየሰጡ የተከፋፈሉ የሃይማኖት ድርጅቶች ተቋቁመዋል ። ቢሆንም አንድ ክርስቲያን የእምልኮት ነፃነት ስላለው ከፈለገው ለአንድ የሃይማኖት ድርጅት አባል ይሆናል እንጂ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን አልፎ ለሁለት ለሦስት ቤተ ክርስቲያን አባል መሆን አይገባውም ይህ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ የተወገዘ ነው ። ሰለስቱ ምዕትም በአንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ብለው በሃይማኖት ጸሎት እንዳስተማሩን እኛም ተከታዮቻቸው የምናምነውና የምንስተምረው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ነው እንጂ አንድ ሰው ለሁለት አብያተ ክርስቲያናት አባል ይሁን ብለን አይደለም ስለዚህ የመልሳችን ማጠቃለያ አንድ ክርስቲያን አባል መሆን የሚገባው ለአንዲት ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነው የሚለው ነው ፡

አቶ መስፍን በአራተኛው ጥያቄ ባልና ሚስት በአንድ ላይ እየኖሩ ባልየው ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባል ሲሆን ሚስቱ ለሌላ ቤተ ክርስቲያን አባል ለመሆን ትችላለች ወይ ? የሚል ጥያቄ አቅርበዋል በመሠረቱ ባልና ሚስት አንድ አካል ናቸው እንጂ ሁለት አካላት አይባሉም ይህ ከሆነ ለአንድ ቤተ ክርስቲያን እንጂ ለሁለት አባል መሆን አይገባቸውም አንድ አካል ስለመሆናቸውም የማቴ ወንጌል ፲፱፡ ፭ ፮ ፡ የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት አንደኛ ቆሮንቶስ ፯፡፬ ይመለከቱ ።

በአምስተኛው ተራ ቁጥር ያቀረቡት ጥያቄ እጅግ በጣም ተራላጊና ሁሉንም የሚያስቸግርና የሚያሳዝን ጉዳይ ነው ምእመናን ለቤተ ክርስቲያን የእርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉት ከትምህርት ባገኙት መንፈሳዊ ግዴታ ነው እንጂ ኮሚቴዎች በሚያደርጉት ልመና አለመሆኑ የታወቀ ነው አንዳንድ ኮሚቴዎችና የሰበካ ጉባኤ ተመራጮች ግን በትምህርት አያምኑም ባለማመናቸውም የትምህርተ ወንጌሉን ጊዜ ከልክለው ምእመናኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን በሚገቡበት ጊዜ እርዳ ይህንን ሥራ ጀምረናል ወደፊትም እንደዚህ ያለ ሥራ ለመሥራት አቅደናል በማለት ሲቀትቱ ይሰማሉ። ርዳታ መጠየቃቸው ባልከፋም ነበር ትምህርተ ወንጌል እንዳይሰጥ እንቅፋት መሆናቸው ግን ሊወገድ

(ወደ ገጽ ፫ የዞረ)





www.ethiopianorthodox.org

# ሦስቱ አባቶች

ፀቅዱስ መጽሐፍ ብዙ ቅዱሳን አባቶች ተመዝግበው ታሪካቸውን እንመለከታለን ፤ የእነርሱም ታሪክ ለተተኪው ትውልድ ሁሉ ትምህርትን ሲሰጥ ይኖራል ።

በታሪካቸው ከታወቁትም አባቶች መካከል አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብ ይገኛሉ ። የእነርሱም መታሰቢያ ዕለት ነሐሴ ፳፰ ቀን መሆኑ የታወቀ ነው የመታሰቢያ በዓላቸውን ዕለት ምክንያት በማድረግ የሦስቱንም አበው ታሪክ በአጭር በአጭሩ ለአንባብያን እናቀርባለን ።

## አብርሃም

ከሦስቱ አበው የመጀመሪያው አብርሃም ነው የአብርሃም ወላጅ አባቱ ታራ ይባላል ፤ ጣዖት አምላኪ ነበር ጣዖት እየጠረበ ያንን ወደ ገቢያ እየወሰደ በመሸጥ ይተዳደር ነበር ፤ ከዕለታት አንድ ቀን ለልጁ ለአብርሃም የተጠረበ ጣዖት አስይዞ ሺጠህ ና ብሎ ወደ ገቢያ ላከው አብርሃምም የአባቱን ፈቃድ ለመፈጸም ጣዖቱን ተሸክሞ ወደ ገበያ ሄደና ዓይን እያለው የማያይ ጆሮ እያለው የማይሰማ እግር እያለው የማይራመድ እጅ እያለው የማይዳሰስ ጣዖት የሚገዛ የለምን ? እያለ ገቢያ ለገቢያ ሲንከራተት ያዩትና የሰሙት ሁሉ ባለቤቱ ያቃለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደሚባለው እርሱ ያቃለለውን ጣዖት ግዙኝ እያለ የሚናገረውማን ሊገዛው ነው ? በማለት እያፌዙ አልገዛው አሉ ።

አብርሃም ያነኑ ጣዖት ተሸክሞ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ ከመንገድ እጅግ በጣም ራበው ፤ ውኃም ጠማው ዕርቦኛልና ምግብ አብላኝ ጠምቶኛልና ውኃ አጠጣኝ የአባቴ አምላክ ! በማለት ቢጠይቀው የማያበላው የማያጠጣው ፡ ሆነ ፤ የራበውንና የጠማውን ሰው ሲያነጋግሩት ራኀቡና ጽሙ ይታገሥለታልና ባይሆንም አነጋግረኝ ቢለው መልስ የማይሠጠው ሆነ ፡ እኔን ቢቸግረኝ ነው እንጂ አንተማ በዕለተ ሰሉሥ የተፈጠርክ እንጨት አይደለህምን ብሎ ከትከሻው አወረደና ቀጥቅጦ ጣለው ወዲያው ምርምር ይጀምራል ።

ነፋስ ኀያል ነው ገለባውን ከፍሬ ይለያል ፤ ባሕርን ይገሥፃል ዕፀዋትን ያወዛውዛል አለና በነፋስ ላምልክ ? አለ ነገር ግን ነፋሱን አለፍ ጠፈር ደፈር ኮረብታ ጋራ ሲጋርደው ተመለከተ ይህ ሕፀፅ አለበት አለና ይህንን ትቶ ውኃ ያደፈውን ያጠራል አትክልትንና አዝርዕትን ያለመልማል የጠማውን ያረካል ብሎ በውኃ ላምልክ ? አለ ግን ውኃን በጭቃ በአፈር ገድበው ወደፈለጉበት ቦታ ሲወስዱት ስላየ ጉድለት መኖሩን ተረዳ እርሱን ትቶ እሳት ኀያል ነው የደረቀውን ያቃጥላል የረጠበውን ያደርቃል የበረደውንም ያሞቃል ብሎ በእሳት ላምልክ ? አለ ነገር ግን እሳቱንም በውኃ ሲያጠፉት ስለአየ እርሱን ተወና በፀሐይ ላምልክ ? አለ ፀሐይንም የተሚላ ሆኖ አላገኘውም ፡ ሌሊት ሲፈራረቀው ማታ ሲጠልቅ ተመለከተ ። ከዚህ በኋላ አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ ሲል የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ወደ ሆነው አምላክ ልመናውን አቀረበ ።

እግዚአብሔር አምላክም ለአብርሃም ከሀገርህ ውጣ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይና እኔ ወደማሳይህ ምድር ሒድ ታላቅም ሕዝብ አደርግሃለሁ እባርክህም አለሁ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ትሆናለህ የሚባርኩህን እባርካለሁ የሚረግሙህንም እረግማለሁ የምድር ነገዶች ሁሉ በአንተ ይባረካሉ አለው ።

ይህንን ቃል አብርሃም ከፈጣሪው በሰማ ጊዜ አልተጠራጠረም ልዋል ልደርም አላለም ፤ ወዲያው ከዘመዶቹ ተለይቶ ከሀገሩ ወጣ ። ያን ጊዜ አብርሃም የ፸፭ ዓመት አዛውንት ነበር ወደምድረ ከነዓንም ገባ ዘፍ ፲፪/፩—፭ ።

አብርሃም እጅግ ባለጸጋ ነበር በከብት በወርቅ በብር የበለጸገ ከመሆኑም ሌላ እግዚአብሔር በሰጠው ሀብት ሳይመካ እንግዳ ይቀበል የተራበ ያበላ የተጠማ ያጠጣ የታረዘ ያለብስ ነበር ከሣራ ልጅ ስላልወለደ ያዝን ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን እግዚአብሔር ለአብርሃም በራዕይ ተገልጾ ወደ ተራራ ይዞ ወጣና ወደሰማይ ቀና በልና የሰማይ ከዋክብትን ቁጠር አለው ፤ እርሱም ለመቁጠር አልችልም ባለው ጊዜ ዘሮችህ እንደዚህ ይበዛሉ ፤ አለው ፤ እንዲሁም ወደ ባሕር ይዞ ወርዶ አሸዋውን ቁጠር ብሎ ጠይቆ ለመቍጠር አልችልም ባለው ጊዜ ዘሮችህ እንደዚህ ይበዛሉ በማለት የብዙ ሕዝብ አባት መሆኑን አረጋግጦለታል ዘፍ ፲፫/፲፮

አብርሃም ከደግነቱና እንግዳን ተቀባይ ከመሆኑ የተነሣ ሥላሴን ለማስተናገድ በቅቷል ፤ ሥላሴም ከቤቱ ገብተው ከተስተናገዱ በኋላ ልጅ እንደሚወልድ አብሥረውት ሄዱ በዓመቱ ልጅ ወልዶ የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ሠይሞታል ።

ይስሐቅ ማለት ደስታ ነው ከ፻፳ ዓመት በኋላ ይህንን ተወዳጅ ልጁን እንዲሠዋ እግዚአብሔር አዘዘው አብርሃም የፈጣሪውን ትእዛዝ ተቀብሎ ልጁን ይስሐቅን ለመሠዋት ተዘጋጅቶ መሠውያውን ይዞ ለመሠዋት እጁን ሲዘረጋ አብርሃም አብርሃም የሚል ድምፅ ሰማና ቀና ቢል ቀንዶቹን በነጭ ሐረግ የታሠረ በግ ከወደሰማይ ሲወርድ ተመለከተ በዚያን ጊዜ ልጁን ይስሐቅን ትቶ በጉን ሠውቷል ፡ ይህም ሃይማኖቱን ፍጹም ሊያደርግለት ችሏል ።

## ይስሐቅ

ከሦስቱ አርእስተ አበው ሁለተኛው ይስሐቅ ነው መልካም ዕንጨት መልካም ፍሬን እንደሚያፈራ በሃይማኖቱና በምግባሩ ከተወደደው አብርሃምም የተወለደው ይስሐቅ የሚሠራው ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ነበር ።

ከላይ እንደተገለጸው አባቱ አብርሃም ለመሥዋዕት ባቀረበው ጊዜ ዕድሜው ፻፳ ነበር አባቱ እርሱን ለመሠዋት ሲዘጋጅ ትንሽ ቅር አላለውም በሙሉ ልብ ፈቃደኛ ስለነበር በልቡ አስተኝቶ እንዲሠዋው ለአባቱ አብርሃም ነገረው ። እግዚአብሔርም ቁርጥ ሕሊናውንና ፈቃደኝነቱን ተመልክቶ በእርሱ ፈንታ በግ እንዳወረደለት ከላይ ተገልጿል ።

ይስሐቅ ፵ ዓመት ሲሆነው ርብቃን አገባ ነገር ግን መካን ሆነችበት ፡ ልጅ እንዲያገኝ ወደ እግዚአብሔር ለመነ እግዚአብሔርም ልመናውን ሰማው ሚስቱ ርብቃም ፀነሰች የፀነሰችው መንታ ስለነበር ጤና ከማጣቷ የተነሣ እግዚአብሔርን በጸሎት ጠየቀች ፤ እግዚአብሔርም ሁለት ልጆች በማኅፀኗ እንዳሉ አስረድቶ ታላቁ ለታናሹ ይገዛል አላት ርብቃም መዋዕለ ዕንሷ ተፈጽሞ መንታ ወለደች ።

በመጀመሪያ የተወለደው ኤሳው ሁለተኛው ያዕቆብ ተብለው ተሠየሙ ፤ ልጆቹ ሲወለዱ ለይስሐቅ ፷ ዓመቱ ነበር ለሁለቱም የተለያየ ስጦታ ነበራቸው ኤሳው አደን የሚያውቅ ሲሆን ያዕቆብ በግ ጠባቂ ነበር ። ኤሳው አውሬ እያደነ እያመጣ ስለሚያበላው ይስሐቅ ኤሳውን ይወዳል ርብቃ ግን የምትወደው ያዕቆብን ነው ወጥ እየሠራ በቅርብ ስለሚያገለግላት ነው ።

ይስሐቅ በሸመገለ ጊዜ ኤሳውን አውሬ አድነህ አምጣና ያነን በልቼ ልመርቅህ ስላለው ተነሥቶ ለአደን ወደበረሃ ሔደ ርብቃ ይህንን ሰምታ ያዕቆብን የበግ ጠቦት አርዶ አወራርዶ ለአባቱ በማቅረብ ከኤሳው ቀድሞ እንዲ[illegible]ረቅ አደረገችው ።

በዚያ ዘመን ረኃብ ጸንቶ ስለነበር ይስሐቅም ወደፍልስጥኤም ንጉሥ አቤሜሌክ ሔደ እግዚአብሔርም ለይስሐቅ ተገልጾ ወደ ምስር አትውረድ እኔ በምነግርህና በማሳይህ ምድር ተቀመጥ እንጂ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ እባርክህማለሁ ይህችን ምድር ሁሉ ለአንተ እሰጣለሁና ለዘርህም ለአብርሃም ለአባትህ የማልሁትን መሐላ እፈጽማለሁ ፡ ዘርህንም እንደሰማይ ከዋክብት አበዛልሃለሁ የምድርም አሕዛብ በዘርህ ይባረካሉ አለው ። እግዚአብሔርም ባረከው ይስሐቅ የአባቱን የአብርሃምን አሠረ ፍኖት ተከትሎ መልካም ምግባርን ከሃይማኖት ጋር አጣምሮ ሲሠራ ኑሮ በ፩፻፹ ዓመቱ አርፎአል ። ኦሪ.ዘፍ፡፴፭.፳፰

## ያዕቆብ

አርእስተ አበው ተብለው ከሚጠሩት ሦስት አባቶች በሦስተኛ ደረጃ ስሙ ተመዝግቦ የሚገኘው ያዕቆብ ነው በአባትም ሆነ በእናት ከእርሱ የማይለይ ኤሳው የሚባል ወንድም ነበረው እናታቸው ርብቃ በአንድነት ፀንሳ በአንድነት ወልዳቸዋለች መንቶች ስለነበሩ በዕድሜ አይበላለጡም ነገር ግን በሚወለዱበት ጊዜ ኤሳው ቀድሞ ስለተወለደ ብኩርናው የተሰጠው ለእርሱ ነበር በኦሪቱ ልማድ በመጀመሪያ የተወለደ ልጅ ሁሉ ቀጥለው ለሚወለዱት ልጆች በኩር መሆን የተለመደ ነበርና ከላይ እንደተገለጸው ለሁለቱም ልጆች የተለያየ ስጦታ ነበራቸው ኤሳው አውሬ ማደን ሲችል የያዕቆብ ስጦታው በግ መጠበቅ ነበር ኤሳው አውሬ እያደነ እያመጣ ስለሚመግበው ይስሐቅ ኤሳውን ይወድ ነበር ርብቃ ግን ከኤሣው ይልቅ ያዕቆብን ትወዳለች ወጥ በመሥራት ያገለግላት ነበርና ።

ከዕለታት አንድ ቀን ኤሳው አደን ውሎ ርቦት ወደቤት ሲመለስ ያዕቆብን የምስር ንፍሮ እየበላ ስላገኘው እባክህ አብላኝ አለው ብኩርናህን ስጠኝና ላብላህ አለው ፡ እርሱም በዚህ ብኩርና ምን ጥቅም አገኝበታለሁ አብላኝና ውሰደው በማለት ብኩርናውን ለወንድሙ ለያዕቆብ በምሥር ንፍሮ ሸጧል ።

ይህም ለጊዜያዊ ጥቅም ከፍተኛ ዋጋ ያለውን ክብራቸውን ለሚሸጡና ለሚለውጡ ስግብግ





www.ethiopianorthodox.org

ቦች ሰዎች በትምህርት መልክ ሲሰጥ ይኖራል ፡ ይስሐቅ በሸመገለ ጊዜ ኤሳውን አውሬ አድነህ አምጣና በልቼ ልመርቅህ አለው ርብቃ ይህንን ቃል ስለሰማች ያዕቆብን ጠርታ ከምትጠብቃቸው በጉች አርደህ አወራርደህ አምጣና እኔ አዘጋጅቼ ሰጥቼህ አብላና ተመረቅ አለችው ያዕቆብ እናቱ እንዳለችው አዘጋጅቶ በማቅረብ ከወንድሙ ኤሳው ቀድሞ የአባቱን በረከት ተቀበለ ፡ ከዚህም የተነሣ ሁለቱ ተጣሉ በይበልጥ ኤሳው በመጀመሪያ ብኩርናውን ሁለተኛም በረከቱን ስለተነጠቀ ያዕቆብን ለመግደል ፡ ይፈልገው ጀመር ወላጆቹ ይህንን ስለዓወቁ ወደ አጐቱ ላባ እንዲሄድ መከሩት ያዕቆብም የአባቱን ምክር በመስማት ከቤርሳቤህ ወጥቶ ወደ ካራን ሲሄድ ሎዛ ከምትባል ቦታ በደረሰ ጊዜ ስለመሸበት ድንጊያ ተንተርሶ ተኛ ሌሊት በሕልሙ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ በዚያች መሰላል መላእክት ሲወጡባት ሲወርዱባት ተመለከተ ።

ያዕቆብ ጧት ከዕንቅልፉ ነቅቶ ከመኝታው ተነሥቶ በእውነት እግዚአብሔር ከዚህ ነው እኔ አላውቅም ነበር አለና ተንተርሶት የነበረውን ድንጊያ አቁሞ በላዩ ላይ ዘይት አፍስሶ ያንን ስፍራ ቤቴል ብሎ ሠይሞታል ። ቤተ እግዚአብሔር ማለት ነው ከዚያ በፊት ግን የዚያ ቦታ ስም ሎዛ ይባል ነበር ቀጥሎም እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን በዚህችም በምሔድባት መንገድ ቢጠብቀኝ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ ወደአባቴም ቤት በጤና ብመለስ ከሰጠኸኝ ሁሉ ለአንተ ከአሥር አንድ እሰጥሃለሁ በጉቶቹን እየጠበቀ ለሰባት ዓመታት ያህል ከኖረ በኋላ ልጁን ድሮለታል ።

ለሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ተገልጾ እንግዲህ ወዲህ ስምህ ያዕቆብ ተብሎ አይጠራ እስራኤል ተብሎ ይጠራ እንጂ ብሎ ስሙን እስራኤል ብሎ ከጠራው በኋላ እኔ እግዚአብሔር ሁሉን የምይዝ ነኝ ለምልም ብዛ ምየ ሕዝብ የአሕዛብም ብዛት ከአንተ ይሆናሉ ነገሥታትም ከወገብህ ይወጣሉ ለአብርሃምና ለይስሐቅም የሰጠኋትን ምድር ለአንተ እሰጣለሁ ከአንተ በኋላም ለዘርህ ምድሩን እሰጣለሁ ብሎ ነግሮት እግዚአብሔር አምላክ ከእርሱ ተሠውሯል ዘፍ ፴፭.፲፫

ያዕቆብ የ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል አባት ለመሆን የበቃ የተባረከ ደግ ሰው ነው ከእርሱ ወገን ክርስቶስ እንደሚወለድ በለዓም የተባለው ፈላስፋ ተገልጾለት "ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ ወየአትት ኃጢአተ እምእስራኤል ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል ክርስቶስ ከያዕቆብ ወገን ይወለዳል ኃጢአትም ከእስራኤል ይወገዳል በማለት ትንቢት ተናግሯል ኦሪት ዘኁ ፳፬.፲፯

ያዕቆብ ጊዜ ሞቱ በቀረበ ጊዜ ልጆቹን ሰብስቦ ከባረካቸው በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል በዚህ ዓለም የኖረውም ፩፻፵፯ ዘመን ነበረ ።

የሦስቱን አበው ታሪክ በአጭሩ ለአንባብያን አቅርበናል ከእነዚህ አባቶች ብዙ ትምህርቶችን ለመቅሰም እንችላለን ሦስቱም በሃይማኖትና በምግባር ፍጹማን ናቸው በዚህም ለአባቶች ሁሉ የበላይነትን መዓርግ ተቀዳጅተዋል ። እንኳን ለወለዷቸውና ለዘሮቻቸው እንደ እነርሱ ያለ ሥራ ለሚሠሩ ሁሉ መመኪያ ሆነው ይኖራሉ ፡ እግዚአብሔር አምላክም እንኳን እኔ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነኝ በማለት ደግነታቸውን መስክሮላቸዋል ፡ ቀሳውስትም የሞቱትን ወገኖች ነፍሳት በአብርሃም በይስሐቅ በያዕቆብ አጠገብ ያስቀምጥልን በማለት ምዕራገ ጸሎት የሚያደርጉት ክብራቸው በዚህ ዓለም ብቻ ሳይወሰን በሰማይ በእግዚአብሔር መንግሥትም ቦታ እንዳላቸው ለማረጋገጥ ነው ።

ይህ ዓለም የተሰጠው ለሁላችንም ነው በዓለም ለሁልጊዜ የሚኖር ሥጋ ለባሽ አይገኝም ዕድሜው ቢያጥርም ቢረዝምም ሁሉም ይሞታል ። የሚሞተው ግን በሥጋው ነው እንጂ በነፍሱ አይደለም ። ሥጋና ነፍስ በተለዩ ጊዜ የሥጋ ባሕርይ ወደ የወገኑ ይመለሳል ፡ መሬት ወደ መሬትነቱ እሳት ወደ እሳትነቱ ፡ ውኃ ወደ ውኃነቱ ነፋስም ወደነፋስነቱ ይመለሳል ። ነፍስ ግን ሕያዊት ነባቢት ፡ ለባዊት ስለሆነች አትሞትም አትፈርስም አትበሰብስም በዚህ ዓለም በሠራችው ሥራ ጸንታ ትኖራለች ክፉ ሠርታ እንደ ሆን ወደ ዘለዓለማዊ ሥቃይ መልካም ሠርታ ከሆነ ግን ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት ትሄዳለች ።

ሁላችንም ከሥቃይና ከመከራ ለመዳን እንችል ዘንድ እንደተጠቀሱት አበው መልካም ሥራ እንሥራ እነዚህ ሦስት አበው ነሐሴ ፳፰ ቀን በቤተ ክርስቲያናችን ይከበራሉ በእግዚአብሔር አምና በቃል ኪዳናቸው የሚማፀነውን ሁሉ የማዳን ተስፋ ከእግዚአብሔር ተሰጥቷቸዋል ፡ ከእነዚህ ደጋግ አባቶች ረድኤትና በረከት ለመሳተፍ እንችል ዘንድ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን ።

ሌ.ኀ.ልሣነ ወርቅ በዛኅ





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

[illegible] የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴ [illegible] መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴ[illegible] እየዘገበ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴ[illegible] ክር ላቀረበ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረበ ግን ስምንት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ.
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org